ከድህነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ
1ኛ ዙር፡ ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 8

*ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ*

# አዲስ አበባን ማሳደግ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት የተደረገ ጥረት (በተካፋይ አይን)

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
አዲስ አበባ

© ታህሳስ 2001 የደራሲውና የማኅበራዊ ጥናት መድረክ

በአዲስ አበባ የታተመ

**አድራሻ፡**

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
ፖ.ሣ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ፡ (251-11) 629-7888/91
ፋክስ፡ (251-11) 629-7889
ኢ.ሜይል: fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org.et

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን፡- ቆንጅት በለጠ

ISBN 10: 99944-50-18-2
ISBN 13: 978-99944-50-27-5

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከኖርዌይ ቤተ ክርስቲያን እርዳታ ድርጅት፣ ከዴንማርክ ኤምባሲ፣ ከአየርላንድ ኤምባሲና ከእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድዖ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የማጥመን፣ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የማጥመን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ፡፡

# ማውጫ


የመክፈቻ ንግግር ........................................................................ v

ምስጋና ...................................................................................... 1

1. እድገትና ትምህርት ........................................................................ 2

2. አ/አ ማዘጋጃ ቤትና አዲስ አበባን ለማሳደግ የተደረጉ ጥረቶች ............ 8

3. ተጨማሪ የሥራ ልምድ ................................................................. 23

4. የ1966 ዓ.ም. ሥር ነቀል የመንግሥት ለውጥና መዘዙ ...................... 30

5. መደምደሚያ ............................................................................ 35

## የመክፈቻ ንግግር

*ሺፈራው በቀለ*

የዚህ ጽሁፍ ደራሲ፣ ኢንጅንየር ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ ከመጀመሪያዎቹ ድህረ ኢጣልያን ባለሙያዎች ውስጥ አንዱ ነበሩ። አቶ ጌታቸው ከአምቦ እርሻ ኮሌጅ በአጠቃላይ እርሻ ትምህርት የተመረቁት በ1944 ዓ.ም. ነበር። በዚሁ ኮሌጅ ባገኙት የቅየሳ ሙያ የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን ተብሎ በአሜሪካን መንግሥት እርዳታ በተቋቋመው መ/ቤት ውስጥ በረዳት መሐንዲስነት ደረጃ በቀያሽነት በዛው ዓመት ተቀጠሩ። በለቀምት (ስሬ) ቀጥሎም በይርጋዓለም (ወንዶ) የድልድይ ቅየሳ ከአለቃቸው (አሜሪካዊ መሐንዲስ) ጋር በምክትልነት ሲሰሩ ቆዩ። ቀጥሎም በእድገት ከምቦልቻ አሰብ በሚሠራው መንገድ ላይ ዲስትሪክት ኢንጂንየርና የአለም ባንክ ሳመሪ ሺት አዘጋጅ ሆነው እንዲሠሩ ተመድበው በመሥራት ላይ እያሉ ት/ቤት ሲገቡ በፈረሙት ግዴታ መሠረት ወደ እርሻ ሚኒስቴር ተገደው ተመለሱ።

ከዚያም በኋላ የፓይንት ፎር ውሃ ሃብት ልማት በአሜሪካን መንግሥት እርዳታ ሲቋቋም እርሻ ሚኒስቴርን ወክለው አብረው እንዲሠሩ ስለተመደቡ በምክትል ሀይድሮሎጂስትነት ከአሜሪካዊው አለቃቸው ጋር በኢትዮጵያ ባሉት ታላላቅና (በበጋ በማይደርቁ) መለስተኛ ወንዞች ላይ የጥናቱ ተካፋይ ሆነው ሠሩ።

ቀጥሎም ወደ ዋናው መ/ቤት ተጠርተው የመ/ቤቱ የተሽከርካሪ ክፍል ምክትል ሀላፊና በኡንራ ስም በሚጠራው የአሜሪካ የእርዳታ መሥሪያ ቤት ውስጥ ሠሩ። በ1949 ዓ.ም የእስኮላርሺፕ እድል አግኝተው ወደ ምዕራብ ጀርመን ተልከው ጋይዘን ሀይም ራይን በሚገኘው የትምህርትና የምርምር ኢኒስቲትዩት ውስጥ ተመድበው በላንድስኬፕ አርኪቴክቸርና በታውን ፕላኒንግ በዲግሪ ሰለጠኑ።

ጥናታቸውን ከጨረሱ በኋላ በትምህርታቸው ያሳዩትን ጥሩ ውጤትና ትጋት በመመልከት ትምህርት ቤቱ ለአምቦ እርሻ ኮሌጅና ለእርሻ ሚኒስቴር በጻፈው ደብዳቤ ወደ ሀኖቨር ዩኒቨርስቲ ተልከው ዶክትሬታቸውን እንዲቀጥሉ ሀሳብ አቀረበ። በጀርመን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የሚገኘው የትምህርት አታሼም ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ጊዜ ያሳዩትን ትጋት አመስግኖ ወደ ሀኖቨር ሄደው ትምህርታቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ የሚአስፈልጋቸውን ወጭ ዘርዝረው እንዲአቀርቡ ቢጠይቃቸውም መጀመሪያ እስካሁን በተማርኩት መስክ አገሬን ባገለግል ይሻላል በሚል ወስነው ወደ ውድ አገራቸው ተመለሱ።

ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱም በኋላ ምንም እንኳ ወደ ጀርመን ልኮ ያስተማራቸው የርሻ ሚኒስቴር ቢሆንም የበለጠ የሥራ ውጤት ለማሳየት የሚችሉት አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ስለነበር ይኸው መሥሪያ ቤት ቀጠራቸውና ሥራቸውን ወዲያውኑ ጀመሩ። የርሻ ሚኒስቴርም ለአገራቸው እስካገለገሉ ድረስ የትም ቦታ ሄደው መሥራት መብታቸው ነው በሚል አልተቃወማቸውም ነበር።

በማዘጋጃ ቤት ለረጅም ጊዜ ካገለገሉ በኋላ መጀመሪያ ወደ መንግሥት ንብረት ድርጅት ተዛወሩ። በመጨረሻም የብሔራዊ ሀብት ልማት ኮርፖሬሽን ኃላፊ ሆነው እንዲሠሩ ተመድበው ድርጅቱን በከፍተኛ ትጋት መምራትና ማስፋፋቱን ተያያዙት። በዚህ ሁኔታ ነበር አብዮቱ የፈነዳውና ኢንጅንየር ጌታቸውም ለእሥር የተዳረጉት። ደርግ ያለምንም ክስ ለስምንት ዓመት ካሠራቸው በኋላ ለቀቃቸው። እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ማንሳት እፈልጋለሁ። ምንም እንኳ ስምንት ዓመት ሙሉ ያለምንም ጥፋት በእሥር ቢማቅቁም፣ ምንም እንኳ ደርግ ታላቅ ወንድማቸውን ያለምንም ፍርድ ቢገድልም፤ ምንም እንኳ አባታቸው ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል በእስር ቤት ሲማቅቁ በበሽታ ቢሞቱም (ተገቢውን ህክምና ቢያገኙ ኖሮ ቢያንስ በዛ ጊዜ አይሞቱም ነበር)፤ ምንም እንኳን አያሌ ዘመዶቻቸው ልክ እንደሳቸው በእስር ቢንገላቱም ወይም ያለፍርድ ቢገደሉም ኢንጅንየር ጌታቸው ከእስር ከተፈቱ በኋላ ከሚወዷት አገራቸው ተሰደው ውጭ መኖር አልፈለጉም።

ይልቁንም በልዩ ልዩ የግል ወይም አለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ በመሥራት ላይ ይገኛሉ። በዚህም ሊመሰገኑ ይገባል። በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በሙያቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በነጻ እያገለገሉ ይገኛሉ።

ይህ ጽሁፋቸው በጊዜው የነበሩት የአገሪቱ መሪ ላገራቸው ትልቅ ራዕይ የነበራቸው ንጉሠ ነገሥት እንደነበሩ ያሳያል። ከወቅቱም ባለሙያዎች ውስጥ ለአገራቸው አርቀው ለማሰብ የሚጣጣሩ፣ ኢትዮጵያን ለማሻሻልና ለማልማት የሚተጉ ምሁራን እንደነበሩባቸው ያሳውቀናል። ስለዘመኑ የመንግሥት እንቅስቃሴም ተጨማሪ ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዳናል። በመጨረሻም በዘመኑ የነበሩ ሰዎችን አስተሳሰብ (በመጠኑም ቢሆን) ያሳያል ብለን እናስባለን። በነዚህም ምክንያቶች ለወጣቱ ትውልድና በተለይም ለታሪክ ተመራማሪዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለን እናምናለን።

## ምሥጋና

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝን ጥናት እንዳደርግና ጽሁፉንም እንዳዘጋጅ የመረጡኝን ፕ/ር ባህሩ ዘውዴን (የማህበራዊ ጥናት መድረክ ሥራ አስፈጻሚ) እና አቶ ሺፈራው በቀለን (የፕሮግራሙ አስተባባሪ) በጣም አመሰግናለሁ። እነርሱ ባያነሳሱኝና ባያነቃቁኝ ኖሮ ይህንን አይነት ሥራ ለማዘጋጀት አላስብም ነበር። እንዲሁም ጽሁፉን ሂልተን ሆቴል ሳቀርብና በኋላም ለህትመት ሳዘጋጅ የረዱኝን የማህበራዊ ጥናት መድረክ ሠራተኞችን ከልብ ማመስገን እወዳለሁ።

ጌታቸው ማኅተመ ሥላሴ

# FSS Publications List

**[Currently available in stock]**

## FSS Periodical

- *Medrek, now renamed FSS BULLETIN* (Quarterly since 1998)

- *Africa Review of Books* (Managed by FSS for CODESRIA)
  - Vol. 1, No. 1(October 2004)
  - Vol. 1, No. 2 (September 2005
  - Vol. 2, No. 1 (March 2006)
  - Vol. 2, No. 2 (September 2006)
  - Vol. 3, No. 1 (March 2007)
  - Vol. 3, No. 2 (September 2007)
  - Vol. 4, No. 1 (March 2008)

| FSS Discussion Papers | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 9 | *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. 2002 | 20.00 |
| No.10 | *Rural Lands and Evolving Tenure Arrangements in Ethiopia: Issues, Evidences and Policies.* Tesfaye Teklu. 2003 | 20.00 |
| No.12 | *Searching for Tenure Security? The Land System and New Policy Initiatives in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato. 2004 | 20.00 |
| No.13 | *A Comparative Study of Forest Management in Eza District, Gurage Zone, Southern Ethiopia.* Tenkir Bonger. 2005 | 20.00 |

| FSS Monograph Series | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 2 | *Poverty and the Social Context of Sex Work in Addis Ababa: An Anthropological Perspective.* Bethlehem Tekola. 2006 | 40.00 |
| No. 3 | *Democratic Assistance to Post-Conflict Ethiopia: Impact and Limitations.* Dessalegn Rahmato and Meheret Ayenew. 2004 | 25.00 |
| No. 4 | *Development Interventions in Wollaita, 1960s-2000s: A Critical Review. Dessalegn Rahmato. 2007* | 35.00 |
| Special No. 1 | *Lord, Zega and Peasant: A Study of Property and Agrarian Relations in Rural Eastern Gojjam.* Habtamu Mengistie. *2004* | 30.00 |

| Consultation Papers on Poverty | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 3 | *Civil Society Groups and Poverty Reduction*. Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. 2001 | 5.00 |
| N0.5 | *The Private Sector and Poverty Reduction* (Amharic).Teshome Kebede,Mulu Solomon and Hailemeskel Abebe. 2001 | 5.00 |
| No.6 | *Government, Donors and Poverty Reduction.* Mekonnen Manyazewal, William James smith and Jeroen Verheul.2002 | 5.00 |

| Gender Policy Dialogue Series | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 2 | *Gender and Poverty* (Amharic). Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 4 | *Gender Policy Dialogue in Oromiya Region.* Edited by Eshetu Bekele. 2003 | 10.00 |
| No. 6 | *Gender Policy Dialogue in Southern Region.* Edited by Eshetu Bekele. 2004 | 10.00 |

| Consultation Papers on Environment | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.2 | *Environment, Poverty and Gender*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.3 | *Environmental Conflict*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. July 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Economic Development and Its Environmental Impact*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.5 | *Government and Environmental Policy*. Consultation Papers on Environment. 2004 | 10.00 |
| No.6 | *የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል (የሰሜን ሸዋ ገበሬች ተሞክሮ)* Consultation Papers on Environment. May 2004 | 10.00 |
| No.7 | *Environmental Challenges of Contemporary Ethiopia and the Indispensable Role of Indigenous Trees*. Legesse Negash. 2004 | 10.00 |

| FSS Studies on Poverty | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.2 | *Faces of Poverty: Life in Gäta, Wälo.* Harald Aspen. 2003 | 15.00 |
| No.3 | *Destitution in Rural Ethiopia.* Yared Amare. 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Environment, Poverty and Conflict*. Tesfaye Teklu and Tesfaye Tafesse. 2004 | 10.00 |
| No.5 | *Issues in Urban Poverty: Two Selected Papers*. Daniel Kassahun and Meron Assefa. July 2005 | 10.00 |

| ከድህነት ወደ ልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ<br>From Poverty to Development: Intergenerational Transfer of Knowledge | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| **ቁጥር 1** | ***ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴች (1966-1983)::* ሽመልስ አዱኛ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 2** | ***የአባይና የተፋሰሶቹ ዓለም ዓቀፋዊ ችግር።* ዘውዴ ገ/ሥላሴ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 2 | *The Blue Nile and Its Basins: An Issue of International Concern*. [English Version]. Zewde G/Sellassie. 2006. | 10.00 |
| **ቁጥር 3** | ***ትምህርት፣ ባህልና ዕድገት: የትዝታ ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እስከ ዓለም አቀፍ የኤኮኖሚ ተቋማት (1948-1996)::* አስፋው ዳምጤ፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 4** | ***ጆርናሊዝምና እድገት በኢትዮጵያ፤ የግል ትዝታች ከ1952 ጀምሮ:*: ነጋሽ ገ/ማርያም፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 5 | *National Air Carriers as Catalysts for Devleopment: The Case of Ethiopian Airlines (ET)*. Semret Medhane, 2006. | 10.00 |
| 2ኛ ዙር ቁጥር 1 | *አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ ተዋናይ:: ተካ ሌገሶ፣ 1999 ዓ.ም.* | 10.00 |

## 1. እድገትና ትምህርት

*ከሁሉ አስቀድሜ ዛሬ ምሁራን ፊት ተገኝቼ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጊዜ የነበረውን የአሠራር ሁኔታ እንዳስታውሳችሁ እድሉን ለሰጠኝና ስብሰባውንም ላዘጋጀው ለማሕበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) መሥሪያ ቤትና እንዲሁም ለናንተ በስብሰባው ላይ ለተገኛችሁት ለተከበራችሁ እንግዶች ከፍ ያለ ምስጋናዬን በትህትና አቀርባለሁ።*

*በዛን ዘመን የነበረውን የአሠራር ሁኔታና የሥራ ውጤት በብዙ መልክ መግለጽ ይቻላል። ለአቀራረቡ የተሻለ ይሆናል ብዬ የመረጥኩት እኔ እራሴ በነበርኩበት ዘመን በነበረው ሕግ በሠራሁበትና እንዲሁም ተጨባጭ ማስረጃ ላቀርብ በምችልበት ላይ ብቻ ቢሆን የበለጠ አሳማኝነት ይኖረዋል ብዬ በማመን በራሴ ልምድ ላይ አተኩራለሁ።*



*ጥንት አባቶቻችን ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ እንዲሉ እኔም ትንሽ ወደኋላ በመመለስ ከተወለድኩበት ከ1921 ዓ.ም. ጀምሮ ስለነበረው ሁኔታ መግለፁን መረጥኩ። የተወለድኩት በ1921 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሲሆን በዘመኑ የነበረው ህብረተሰብ ማንኛውም ልጅ ስነምግባር ያለው ሆኖ እንዲያድግ የሚያደርገውን ጥረት ማስታወስ እፈልጋለሁ።*

*ለህጻናት የስነ ምግባር ትምህርት መስጠት የሚጀምረው ልጁ ገና ሕፃን ሆኖ እሳት እንኳን እንደሚፈጀው ከማያውቅበት እድሜ ጀምሮ ነበር። በተከታታይም እድሜአችንን እየመጠኑ አቅማችን የሚችለውን ዓይነት ሥራዎች ጭምር ያሠሩን ነበር። ወጣቱ ትውልድ በሥነ ምግባር ታንጸ እንዲያድግ ምክርና*

| | | |
|---|---|---|
| 2ኛ ዙር ቁጥር 2 | *በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት፡፡ ጠና አበረ፣ 1999 ዓ.ም.* | 10.00 |
| 3ኛ ዙር ቁጥር 3 | *የኢንዱስትሪና የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር እድገት፡፡ ተፈራ ኃ/ሥላሴ 1999 ዓ.ም.* | 10.00 |
| 3ኛ ዙር ቁጥር 4 | *የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ምሥረታና ዕድገት፡፡ በትሩ አድማሴ 2000 ዓ/ም፡፡* | 10.00 |
| 3ኛ ዙር ቁጥር 5 | *የባንክ እድገት ለአገሪቱ ልማት ያደረገው አስተዋጽኦ፡፡ ተፈራ ደግፌ 2000 ዓ/ም፡፡* | 10.00 |
| 2ኛ ዙር ቁጥር 6 | *የኢትዮጵያ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ አጀማመርና ሂደት፡፡ አምባሳደር ጥሩነህ ዜና 2001 ዓ/ም፡፡* | 10.00 |

| **Book Series** | Price (Birr) |
|---|---|
| • *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below.* Edited by Bahru Zewde and Siegried Pausewang. Nordic African Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2006 | 80.00 |
| • *Land and the Challenge of Sustainable Development in Ethiopia.* Edited by Dessalegn Rahmato and Taye Assefa. 2006 | 77.00 |
| • *Decentralization in Ethiopia. Edited* by Taye Assefa & Tegegne Gebre-Egziabher . 2007 | 51.00 |
| • *The World of Girls and Boys in Rural and Urban Ethiopia.* Edited by Eva Poluha. Save the Children and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2008. | 50.00 |
| • *Academic Freedom in Ethiopia : Perspectives of Teaching Personnel.* Edited by Taye Assefa. 2008 | 50.00 |
| • *Digest of Ethiopia's National Policies, Strategies and Programs.* Edited by Taye Assefa. 2008 | 100.00 |
| • *የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሐግብሮች ጥንቅር፡፡* አርታዒ ታዬ አሰፋ፣ 2001 ዓ.ም. | 100.00 |
| • *Civil Society at the Crossroads: Challenges and Prospects in Ethiopia.* Edited by Taye Assefa & Bahru Zewde. 2008 | 40.00 |
| • *Society, State and Identity in African History*: Edited by Bahru Zewde. 2008 | 100.00 |

| **Research Report** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | • *Rainwater Harvesting in Ethiopia: Capturing the Realities and Exploring Opportunities. Daniel Kassahun. 2007.* | 25.00 |

| **Environmental Documentaries on CD and Video** | Price (Birr) VCD | Price (Birr) VHS |
|---|---|---|
| • የከተማችን አካባቢ ከየት ወደየት? (Amharic Film) | 50.00 | 100.00 |
| • ውጥንቅጥ ድህነትና የአካባቢያችን መጎሳቆል (Amharic Film) | 50.00 | 100.00 |
| • "Witinkit": Poverty and Environmental Degradation (Amharic with English Subtitles) | 50.00 | 100.00 |

ትምህርት ሰጭዎች ቤተሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ጐረቤትም መንገደኛውም ጭምር ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ አባትና እናቴ እንዲሁም ሞግዚቴ መልካም ባህርይ እንዲኖረኝና ለወግ ለማዕረግ እንድበቃ ስነ ምግባር ያስተምሩኝ ነበር፡፡ ሳጠፋም በምክር፣ ምክራቸውን ካልሰማሁም እንደ ጥፋቴ ክባድነት በኩርኩም፣ በቁንጥጫ፣ ባርጩሜ፣ በአለንጋ መቀጣት እንደ ህግ ስለነበር እንደ ጥፋቴ መጠን ተቀጥቻለሁ፡፡ ሌሎችም ሲቀጡ ሳይ ነግ በኔ ነው እያልኩ ከኔም ሆነ ሌሎቹ ከተቀጡበት ለመታረም በመቻሌ ከተቀጣሁበት ጊዜ ይልቅ የተመረቅኩበት ጊዜ ይበልጥ ነበር፡፡

ምርቃታቸውም፣ እግዜር ይስጥህ፣ እድሜና እንጀራ ይስጥህ፣ ለወግ ለማዕረግ ያብቃህ፣ የዘመድ አውራ ያድርግህና፣ እግዚአብሔር ይባርክህ የሚሉ ነበሩ፡፡ ሥነ ምግባር በቤትም በውጭም ተፈላጊ በመሆኑ መንገድ ላይ ስናጠፋ ብንገኝ የማያውቀን መንገደኛ እንኳን አያልፈንም፡፡ ና አንተ ባለጌ የባለጌ ልጅ ብሎ ጠርቶ በጥፋታችን መጠን ይቀጣን ነበር፡፡ ጥሩም ከሠራን እንመረቃለን፡፡

እኔ አሁንም በፊትም ሳስበው መቀጣቴና መመረቄ ነው ለዚህ ያበቃኝ እያልኩ እስካሁን ቀጭዎቼን አመሰግናለሁ፡፡ በዛን ዘመን ይሰጠን የነበረው ስነምግባር ከአስርቱ ቃላት የተቀዳ ከመምሰሉም በላይ በመንግሥት የታወጀ ይመስል ልጆቹ ሲያጠፉ የማይቀጣ ቤተሰብ ጨርሶ አልነበረም፡፡

በአጠቃላይ ከመልካም አስተዳደግ የተገኘው ውጤት ግብረገብነትና ጨዋነት፣ እራስን በራስ የማስተዳደር ችሎታ እና አገር የመረከብ ክህሎት ያለው ትውልድ በመፍጠሩ በጊዜው የነበረው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት መጠነ ሰፊ አስተዳዳሪዎችና ሕግ አስከባሪ መለዮ ለባሾች አላስፈለጉትም፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያችን ሰፊ፣ ብዙ ሕዝብ ያላትና ከብዙ ጐረቤት አገሮች ጋር የሚአዋስን ረጅም ጠረፍ የነበራት አገር ብትሆንም በስነሥርአት የታነጸው ሰላማዊና አገር ወዳድ ሕዝቧ እንደ ፖሊስና ጠረፍ ጠባቂ ስለሚቆጠር የኢትዮጵያ የፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት ብዛት አርባ አምስት ሺህ ብቻ ነበር፡፡

በዛን ዘመን አንድ ሰው ለኃላፊነት ሥራ፣ ለጋብቻ፣ ለአደራ፣ ለሽምግልና የሚበቃው፣ ምግባረ ብልሹ ያልሆነ ጨዋ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ትምህርት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ መመረጫ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለጌ ምሁር ከሆነ እራሱም አይከበር ሰውንም አያከብር፡፡ ለሠፈርም ጠንቀኛ ነው የሚሆነው፡፡ ባጠቃላይ ለመከበር ሰውን ማክበር ያስፈልጋልና፡፡

በዛን ወቅት አንድ ጊዜ (እንደማስታውሰው) ይህን ያልተገነዘበ ፣ ካለኔ ማን አለ እያለ የሚኩራራ፣ በሰዓት ሥራ የማይገባ፣ ኃላፊነትም የማይሰማው ሰው ስለተገኘ አለቃው ይጠሩና ድክመቱን ገልጠው ማስጠንቀቂያ ሲሰጡት ተቆጥቶ እንዴት እንዲህ ይናገሩኛል እኔ እኮ በዲግሪ ምሩቅ ነኝ ሲላቸው ያለ ሥራ ዲግሪ ከጠቀመህ የኔንም እጨምርልሃለሁ ውሰድና እቤትህ ስቀለው ብለውታል፡፡ ከምግባረ ብልሹ ሰዎች መታወቂያ ዋና ዋናዎቹ ጥጋብ፣ ስንፍና፣ ሥካር፣ ጉቦኝነት፣ ውሸትና አሳባቂነት ናቸው፡፡

በሥራ ላይ ተመድቦ የሚገኝ ባለሥልጣንም ሆነ ተራ ሠራተኛ በተቻለ መጠን በትምህርት ወይም በሥራ በቂ ልምድ ያለው እንዲሆን ግድ ይላል፡፡

*መስፈርቱን የማያሟሉ ሠራተኞች በአንዳንድ ቦታ ተመድበው አይገኙም አልልም፡፡ ነበሩ፡፡ እነዚህም የቀድሞ አገልግሎታቸውንና ውለታቸውን በመቁጠር ወይም ባለሙያ በመጥፋቱ፣ አንዳንዴም በአድልዎ፣ በሥራ ገበታ ላይ ይመደባሉ፡፡ እሱም ሆኖ ሥራው ቢበላሽ ተወቃሽነት ስላለ ቀጣሪው እነዚህን ሰዎች የሚመድባቸው ኃላፊነት በሌለው ዝቅተኛ ቦታ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ሁሉም ሰው ተናጋሪና ተቺ በመሆኑ ወሬው ስለማይደበቅ ታላቅ ፍራቻ ስላለ ዓይን ያወጣ አድልዎና ጥፋት ለመፈጸም ከባድ ነበር፡፡ ወሬውን እስከ ንጉሡ ድረስ የሚአደርሱ የስለላ ተቋሞችም ስለነበሩ ጥንቃቄው የበዛ ነው፡፡*

*ስለዚህ ማንኛውም ሰው በተቻለ መጠን ጥሩ ሠርቶ ለመመስገን፣ ለመሾም፣ ለመሸለምና ደህና ደምወዝ ለማግኘት ይጥር ነበር፡፡ ውድድሩ ከፍተኛ ስለነበር በጥፋት ላለመዘፈቅ እርስ በእርሱ ተጠባብቆና ተባብሮ ለመሥራት ሁልጊዜም ጥረት ይደረግ ነበር፡፡ ውድድሩ ጤናማ ከመሆኑ የተነሣ ማንኛውም ሰው ከመደበኛ ሥራው ውጭ ለአገሪቱ ጠቃሚ ናቸው የሚላቸውን ሃሳቦች እያመነጨና ፕሮጀክት እየቀረጸ እስከ ንጉሡ ድረስ በግሉ የማቅረብ እድል ስለነበረው በዚህ በኩል ሰፊ ነፃነት ነበር ማለት ይቻላል፡፡*

## *የትምህርት ሁኔታ*

*በአገራችን በኢትዮጵያ ትምህርት ለወጣቱ ትውልድ በስፋት ለማዳረስ በአዋጅ ደረጃ የወጣው በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ1898 ዓ.ም ነበር፡፡*

*አዋጁም ባጭሩ ፡-*

> **ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፡-**
>
> **እስካሁን ማንም የእጅ ሥራ አዋቂ የነበረ ሰው በውርደት ስም ይጠራ ነበር፣ ስለዚህም ማንም ሰው ለመማርና ለመሰልጠን የሚደክም አልነበረም፡፡ በዚህ ጉዳይ በሆነ ሁኔታ ብንኖር ቤተክርስቲያኖች ይዘጋሉ፤ ይልቁንም ክርስቲያንነት አይገኝም፡፡**
>
> **በሌሎች አገሮች እያንዳንዱን ነገር ብቻ መማር ሳይሆን አዲስ ነገሮች ይሠራሉ፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊት ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ሁሉ ከስድስት አመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን ልጆቻቸውን ለማስተማር ለማይተጉ ቤተሰቦች ወላጆቻቸው ሲሞቱ ንብረታቸው ለልጆቻቸው መሆኑ ቀርቶ ለመንግሥት ይተላለፋል፣ ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን የሚአዘጋጅው መንግስት ነው፡፡**

*በግርማዊ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥትም ይህንኑ ያፄ ምኒልክን አዋጅ በመከተል በ1921 ዓ.ም ቀጥሎ ያለው የትምህርት አዋጅ ተነግሯል፡፡*

> **ልጅ ያለው ሰው ሁሉ ልጁ ክፉውንና በጎውን የሚለይበትን ንጉሡንና ፈጣሪውን የሚፈራበትን እውቀትን ለማግኘት የንባብና የጽሕፈት ትምህርት ያሳስተማረ መቀጫውን ሃምሳ ብር እየከፈለ የመቀጫውን ገንዘብ ወደ ቤተክርስቲያን እየገባ ለነዳያን ምግብና ልብስ ይሆናል፡፡ የንስሐ አባትም የሆንክ ቄስ ሁሉ የንስሐ ልጆችህ ልጆቻቸውን**

> እንዲያስተምሩ ምከር፡፡ ሁለት ሶስት ጊዜ ልጆቻችሁን አስተምሩ ብለኽ ከመከርክ በኋላ ምክርህን የማይቀበሉ ቢሆን ግን አዋጅ አፍራሾች መሆናቸውን ሳገሩ ሹም አስታውቅ፡፡
>
> የገጠር መሪ ጌታም የሆንክ ሰው ፈጣሪውን አውቆ የሚጠቀምበትን በደብርህ መንፈሳዊ ዕውቀት ስምዕመናን በሚገባው ልክ የስብከት ትምህርት በየደብርህ አስተምረው፡፡ ሳታስተምር የቀረህ እንደሆነ በሹመትህ ተቀጣለህ ለሕይወቱና ለኑሮው የሚሻውን ገንዘብ ለማግኘት እንዳይቸገር ባገራችን ካለው የእጅ ሥራ ልብህ የሚወደውን አንዳንድ የእጅ ሥራ እንዲማር አድርግ፡፡ ለትዳሩ የሚሆን የእጅ ሥራ ሳታስተምረው የቀረህ ከሆነ ግን በአካል ጉዳይ ካሳ ትከፍላለህ፡፡ ይህንንም የተቆጠረውን ትምህርት ይማር የተባለው ልጅ እድሜው ከሰባት ዓመት እስከ ሃያ አንድ ዓመት ድረስ ያለውን ነውና፡፡ ከዚህ በላይ ሳለው የትምህርት እድሜ በተላለፈው ልጅ አባቱ አላስተማርክም ተብሎ አይቀጣም፡፡ የሚል ነበር፡፡

*የአፄ ምኒልክን የትምህርት አዋጅ መሠረት በማድረግ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ያገራችን እና ዘመናዊው የውጭ ትምህርት ጉን ለጉን እንዲሰጡ በማድረጋቸው አገሪቱ ባላት አቅም በተቋቋሙት ትምህርት ቤቶች እየገባን ዘመናዊ ትምህርት ከተማርነው ውስጥ አንዱ እኔ እገኛለሁ፡፡*

*የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በ1938 ዓ.ም አጠናቀቅሁ፡፡ ቀጥዬም የአምቦ ከፍተኛ የእርሻ ትምህርት ቤት (አምቦ አግሪካልቸራል ኮሌጅ) ሲከፈት የመግቢያ ፈተና ወስጄ በዚሁ ዓመት ገባሁ፡፡ የትምህርት ጊዜው ለስድስት ዓመት ሲሆን ሁለቱ ዓመት የዝግጅት ትምህርት ሌላው አራት ዓመት ደግሞ የኮሌጁ ትምህርት የሚሰጥበት ጊዜ ነበር፡፡ የትምህርት ጊዜው የተራዘመበት ዋናው ምክንያት ሁሉንም ዓይነት የእርሻ ዘዴ በስፋትና ጠለቅ ባለ ሁኔታ ለማስተማር ታስቦ ሲሆን ይህም ጊዜ በቂ ባለመሆኑ ከርሻ ጋር ብዙ ግንኙነት ከሌላቸው የትምህርት ዓይነቶች እየተቀነሰ ለእርሻው ትምህርት ይጨመርለት ነበር፡፡*

*ለምሳሌ፡- ስለ እርሻ ስንማር የእርሻ መሣሪያዎችን አጠቃቀም፣ ትራክተሮችን መጠገን፣ የአስተራረሱን ሁኔታ ማወቅ ስለመስኖ ስንማር የቅየሳ ትምህርትን ጠንቅቆ ማወቅ፣ ስለከብት እርባታ ስንማር ሕክምናውንም ማከናወን እንድንችል ተገቢው ስልጠና ይሰጠን ነበር፡፡ ሌሎችም የትምህርት ዓይነቶች በተመሣሣይ መንገድ ይሰጡ ነበር፡፡ በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ባገኘነው የእውቀት ደረጃ በአጠቃላይ የእርሻ ባለሙያ (ጀኔራል አግሪካልቸራሊስት) ተብለን በ1944 ዓ.ም ተመረቅን፡፡*

*በመሠረቱ የተሰጠን ትምህርት ለዲግሪ የሚያበቃ ሁኖ ሳለ የእርሻ ሚኒስቴር የትምህርት ቤቱን ደረጃ ለትምህርት ሚኒስቴር ባለማሳወቁ በተፈጠረው ችግር ምክንያት የኛ የተማሪዎቹ እድል ተሰናክሎ የኮሌጅ ዲኘሎማ በሚል ተወሰነብን፡፡*

## የሥራ ዓለም

በእርሻ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እስከምደለደል ድረስ ሥራ እንዳልፈታ በማሰብ ትምህርት ቤት እያለሁ በቀየሳ ሞያ ለማገልገል በአሜሪካኖች ይመራ ለነበረው አውራ ጐዳና ባለሥልጣን (Imperial Highway Authority) ማመልከቻ ጽፌ ስለነበር በረዳት መሀንዲስነት (Engineer/Aid) ቀጠሩኝ፡፡

ወዲያውኑ ወለጋ ተመድቤ የድልድይ ቅየሳ ሥራ ከአሜሪካዊ አለቃዬ ጋር መሥራት ጀመርኩ፡፡ የሥራን ከባድነት ማወቅ የጀመርኩት እዚያ ነበር፡፡ በትምህርት ያገኘሁትን እውቀት በሥራ ላይ ለማዋል ያለውን ችግር ከነ መፍትሔው የተማርኩትም በዛን ወቅት ነበር፡፡

አንድ ቀን ገደላማ በሆነ ቦታ ላይ ቲዎዶሊት የተባለ መሣሪያ ሌቭል አድርጌ ለመሥራት ስዘጋጅ ውሃልኩ እየተዛባ አስቸገረኝ፤ ምክንያቱም መሬቱ ስራስር የበዛው የሚአረገርግ በመሆኑ ነው፡፡ አቅሜ የቻለውን ያህል ትራይፖዱን ረገጥኩ፡፡ አሁንም አልሆነም፡፡ ይሄ ሁሉ ሲሆን አለቃዬ ይመለከቱ ኖሮ መጡና ትልቁ ትምህርት ቤት ሥራ መሆኑን አወቅህ አይደል በል ችካሎች ቁረጥና ትራይፓዱን በምታቆምበት ቦታ አጥብቀህ ቸክለህ ቅበርና ሲጠብቅ እዛ ላይ አቁም አሉኝ፡፡ ያሉኝን አድርጌ ሠራሁ፡፡ ከዚያ በኋላም ብዙ ትምህርት እየሰጡ አሰለጠኑኝ፡፡ ቀጥሎም ለተመሣሣይ ሥራ ወደ ይርጋለም ወንዶ አብሬአቸው ሄድኩ፡፡ ለኔ ሥራም ትምህርትም ነበር፡፡ ለጥቂት ቀናት ፈቃድ ጠይቄ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ እረፍት ላይ እያለሁ አስቸኳይ ቴሌግራም ደረሰኝ፡፡ ቴሌግራሙም ከኮምቦልቻ ወደአሰብ ወደሚሠራው የአስፋልትና የድልድይ ሥራ ፕሮጀክት ተዛውረህ የዲስትሪክቱን የምህንድስና ሥራና የአለም ባንክ ሪፖርት አዘጋጅ ሁነህ ሥራ የሚል ነበር፡፡ ሌላ አማራጭ ስላልነበረኝ ትዕዛዙን ተቀብዬ ወደዛ ተዛወርኩ፡፡ ሁለቱም ሥራ ለኔ አስቸጋሪ አልሆነብኝም፡፡ እንዲያውም አለቃዬ አመስግነው በጥቂት ወራት ውስጥ ደምወዜን በእጥፍ ያህል አሳደጉልኝ፡፡

በሥራዬ ተደስቼ በመሥራት ላይ እያለሁ በመስሪያ ቤቱ በኩል ከእርሻ ሚኒስቴር አንድ ደብዳቤ ደረሰኝ፡፡ የደብዳቤውም ይዘት «የእርሻ ትምህርት ቤት ስትገባ ትምህርትህን ስትጨርስ ለሁለት አመት አገለግላለሁ በማለት የፈረምከውን ግዴታ አላከበርክም፤ አሁንም ባስቸኳይ እንድትመጣ» የሚል ነበር፡፡

የገባሁትን ግዴታ ለማክበር ስል የምወደውን ሥራና ደህና ደመወዝ ትቼ ወደ እርሻ ሚኒስቴር ተመለስኩ፡፡ ከዛም በአሜሪካን መንግሥት እርዳታ ተቋቁሞ ወደነበረው ፓይት ፎር ዋተር ሪሶርስ መሥሪያ ቤት እርሻ ሚኒስቴርን ወክዬ እንድሠራ ተላክሁ፡፡ እዛም በሐይድሮሎጂ ክፍል የኤክስፐርቱ ምክትል ሆኜ ተመደብኩ፡፡ አሜሪካዊው አለቃዬ ታላቅ ምሁር ስለነበሩ እኔን ከሥራው ጋር ለማስተዋወቅና ለማስተሳሰር የነበራቸው ፍላጐት ከሚጠበቀው በላይ ነበር፡፡ ዋናው ሥራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ትላልቅና ታናናሽ ወንዞች ጠቅላላ ሁኔታ ማጥናት ነበር፡፡

በነዚህ ወንዞች ዳርቻ መሣሪያዎችን በመትከል የውሃውን ከፍታና ብዛት በመመዝገብ፣ በሌሎችም መሣሪያዎች የውሃውን ፍጥነት፣ አጥቦ የሚወስደውን

የአፈር አይነትና ብዛት፣ የአየሩን እርጥበት፣ የነፋሱን ኃይልና አቅጣጫ፣ የዝናቡን ብዛት፣ የሙቀቱን መጠን በመከታተል ውጤቱን እግድብና ሌላም አገልግሎት ላይ ለሚአውሉት ክፍሎች እንሰጥ ነበር፡፡ እነዚህን ወንዞች ስናጠና ብዙ ችግሮችን በመጋፈጥ ነበር፡፡ የመንገድ፣ የነዳጅ፣ የሆቴል፣ የማደሪያ፣ የውሃ፣ የወባ፣ የዱር አራዊት፣ የእባብና ዘንዶ፣ የጤንነት ችግሮችን በመቋቋም ስንሠራ ለሥራ ውጤታችንም ከፍተኛ ዋጋ እንሰጠው ነበር፡፡

ለምሳሌ የቆቃ ግድብን በምናጠናበት ጊዜ በውሃ ብወሰድም በአጋጣሚ ከአንድ ግንድ ላይ ሲያጋጩኝ ግንዱን አቅፌ በመያዜ ነፍሴን ማትረፍ ችያለሁ፡፡ የመኪና አደጋም አጋጥሞን ተርፈናል፡፡

እንደገና በእድገት መልክ ወደ እርሻ ሚኒስቴር ተዛውሬ በዋና መስሪያ ቤት የተሽከርካሪ ክፍል ምክትልና ኡንራ የተባለው የአሜሪካን መንግሥት እርዳታ ድርጅት ለሰጣቸው ትራክተሮችና የእርሻ መሣሪያዎች ኃላፊ በመሆን መሥራት ጀመርኩ፡፡

መሣሪያዎቹ አዲስ ዓይነት ስለነበሩ ለተጠቃሚዎቹ እቃውን ማለማመድና ማሠልጠኑ ቀላል አልነበረም፡፡ እሱንም የዘመኑን የእርሻ ዘዴ ለማስተማሪያነት በሰፊው ተጠቅመንበታል፡፡

## *ለከፍተኛ ትምህርት እስኮላርሺፕ*

እርሻ ሚኒስቴር በመሥራት ላይ እያለሁ ከምዕራብ ጀርመን እስኮላርሺፕ በመገኘቱ ከብዙ ጓደኞቼ ጋር ተመርጨ ወደ ጀርመን እንድንሄድ ተወሰነ፡፡ ለመንገዳችንም ሁለት የሱፍ ልብስ፣ ወፍራም ካፖርት፣ ባርሜጣ፣ አንድ ጥንድ ጓንቲ፣ አራት ሸሚዝ፣ ካናቴራ፣ ሙታንታ፣ ክራባት፣ ሁለት ጥንድ ጫማ፣ የቤት ጫማ፣ መሐረቦች፣ የግር ሹራቦች፣ ፒጃማና ሌላም በመንግሥት ወጪ ተገዛልን፡፡ በመጨረሻም የኪስ ገንዘብ ተሰጥቶን በአውሮፕላን ተሳፍረን ተላክን፡፡ ከዛ በኋላ ሁሉም የኛ ጣጣ ሆነ፡፡

ሁላችንም ካለማወቃችን የተነሳ የምናደርገው ስህተት ከሌላው ተመልካች የበለጠ እራሳችንን ያስቀን ነበር፡፡ ከመሐከላችን እንኳንስ የውጭውን አለም አኗኗር ይቅርና አዲስ አበባን እንኳን በደምብ የማያውቁ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ በጣም የራበው የምግብ ሊስት ሲቀርብለት ዓይነቱን ስለማያውቅ ሜኑ ላይ ረጅም ስም ያለው ምግብ ብዛት ያለው እየመሰለው ሲያዝ ያልጠበቀው ትንሽ ምግብ ሲመጣለት ተጨማሪ ማዘዝ ተገዷል፡፡ ኮርንፍሌክስ ከወተት ጋር ሲቀርብለት እየዘገነ የቃመም አልጠፋም፡፡ ጊዜው የበረዶ ሰዓት መሆኑን ያላወቀ በዛ በረዶ በነጠላ ጫማ ከአውሮኘላን የወረደም አልጠፋም፡፡ ባርሜጣ አርጐ የማያውቀው ደግሞ ባርሜጣውን በእጁ ይዞ ባርሜጣዬ ጠፋ ፈልጋችሁ አምጡ ብሎ ሆቴሉን ያመሰና በኋላም ሕዝቡን በሳቅ የጨረሰ ቲያትረኛ ነበር፡፡

ከዚህ ሁሉ ስህተት በኋላ መሠልጠን አይቀርምና እየሰለጠንን መጣን፡፡ ዋናው ቁምነገር ግን በትምህርታችን (የቋንቋውንም ከባድነት ተቋቁመን) ሰነፍ የሚባል ተማሪ ጨርሶ አልነበረም፡፡




የትምህርት ቤት ምድቤ ጋይዘንሀይም ራይን ውስጥ በሚገኘው የትምህርትና የምርምር ኢንስቲትዩት ነበር:: ወደዚህ ትምህርት ቤት ከሚመጡት አብዛኞቹ ለፓስት ግራጁዌት ሲሆን የሚመጡትም ከአሜሪካ፣ ከጣሊያን፣ ከስዊድን፣ ከእንግሊዝና ከዩጐዝላቪያ ነው::

የኔ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ለዛ ትምህርት ቤት የሚበቃ መሆኑን ማረጋገጥ ስላልቻሉና ከአፍሪቃም በዚህ ደረጃ ተማሪ ተቀብለው ስለማያውቁ ከአዲስ አበባና ከአምቦ የርሻ ኮሌጅ ማረጋገጫ መጠየቅ ግድ ሆነባቸው::

ከሁለት ዓመት በላይ በሥራ ላይ የነበርኩ መሆኔን የትምህርት ደረጃዬም ለመግባት የሚያበቃኝ መሆኑ ቢገለጽላቸውም ስለተጠራጠሩ በአራት ሰብጀክት ፈተና እንድወስድ አስገድደውኝ ተፈተንኩ:: ውጤቱም በሁለቱ ጥሩ በሁለቱ ደግሞ አጥጋቢ ሆኖ ስላገኙት መደበኛ ተማሪ ሆኜ ተመዘገብኩ:: የትምህርት አይነት የመምረጥ እድሉ ስለተሰጠኝ የምህንድስናው ዘርፍ መርጬ ትምህርቴን ጀመርኩ::

መሠረታዊውን የምህንድስና ሙያ በመማር ላይ ባለሁበት ጊዜ ባገኘሁት ግንዛቤ ለሙያ ምርጫዬ (Specialization) እንደ አንድ ትምህርት ወይም ሙያ ይሰጥ የነበረውን የላንድስኬኘ አርኪቲክቸርና ታውን ፕላኒንግን መረጥኩ:: በዛን ዘመን የታውን ኘላኒንግን ትምህርት በተለይ የሚሠጥ አገር ወይም ዩኒቨርሲቲ በጣት የሚቆጠር ሲሆን እነዚህም ከተቋቋሙ የ50 ዓመት እድሜ አልነበራቸውም:: ይህም ሙያ በብዛት የተወሰደው ከላንድስኬፕ አርኪቴክቸር ሲሆን እነ ቨርሳይና ሌሎችም በውበት የተሠሩ ከተሞች በላንድስኬፕ አርኪቴክቶች ስለሆነ ትርጉሙን ብንመለከት ሁኔታውን ያረጋግጥልናል:: በሙያተኞች እንደሚተረጐመው፣ “Landscape Architecture is the arrangement of Earth and the Objects on it for man’s and its beauty” በግርድፉ በአማርኛ ሲተረጐም «ላንድስኬፕ አርኪቴክቸር መልክአ ምድርን በላይዋ ከሚሠፍሩ ነገሮች ጋር አዘጋጅቶና አስውቦ ለሰው ልጅ ጥቅም የሚያውል ሙያ ነው::» ይለዋል:: በሰለጠነው ዓለም ይህ ሙያ በማንኛውም ሥራ መስክ ተፈላጊነት አለው::

ለማጠቃለል ታውን ፕላኒንግ የሚያተኩረው በአብዛኛው በከተማ አስተዳደርና ኢኮኖሚዋ ላይ ሲሆን የዝርዝር ጥናቱ ዋና ባለሙያዎች አርኪቴክት ፕላነሮችና ላንድስኬፕ አርኪቴክቶች ናቸው።

በዚህ ሙያ ትምህርቴን ባጠናቀቅሁበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ሰኔ 4/1949 ዓ.ም. ደብዳቤ ከእርሻ ሚኒስቴር ደረሰኝ። ቀጥሎም በጀርመን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ካለው የትምህርት አታሼ ስለ ትምህርቴ ሁኔታ የፕሮግሬስ ሪፖርት እንደሚደርሰው ጠቅሶ በውጤቴም ሆነ በፀባዬ መደሰቱን ጻፈልኝ። አያይዞም አሁን በቅርብ ጊዜ በአምቦ ዲሬክተር በኩል የተላከ ደብዳቤ ትርጉም ስለደረሰን አሁን ካለህበት ትምህርት ቤት ትምህርት ካበቃህ በኋላ ወደ ሀኖቨር ዩኒቨርስቲ ሄደህ ከፍተኛ ትምህርት እንድትቀጥል አጥብቀው የትምህርት ቤቱ ዴሬክተር ስላስታወቁን ሀኖቨር በሚገኘው ዮኒቨርስቲ ስትገባ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅብህና ምን ያህል ስንቅና ገንዘብ እንደሚያስፈልግህ የሚአሳይ ዝርዝር በአቶ ከበደ ጽጌ በኩል እንዲደርሰን እንድታደርግ የሚል ነበር።

የእኔ መልስ ግን ኢትዮጵያ ውስጥና አሁንም ጀርመን አገር የተማርኩትን በቅድሚያ አገሬን ለማገልገል ሥራ ላይ ማዋል ስለምፈልግ ወደ ሀኖቨር ሄጄ ትምህርቴን መቀጠል አልፈልግም። ለተደረገልኝ ከፍተኛ ድጋፍ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ የሚል ስለነበር ወደ ኢትዮጵያ መመለሻ የአውሮፕላን ትኬት ተልኮልኝ ወደ ኢትዮጵያ ተመለስኩ።

## 2. አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትና አዲስ አበባን ለማሳደግ የተደረጉ ጥረቶች

ከጀርመን አገር ወደ ኢትዮጵያ ከተመለስኩ በኋላ ምንም እንኳን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ጀርመን የላከኝ የእርሻ ሚኒስቴር ቢሆንም በተማርኩት ትምህርት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት የምችለው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ውስጥ በመሆኑ የሥራ መጠየቂያ ማመልከቻ ለማዘጋጃ ቤት አቀረብኩ። በዛን ዘመን ማንኛውም ምሁር በተማረው ትምህርት ለአገር ጥቅም በሚሰጥ ቦታ ተመድቦ እስከሠራ ድረስ በየትኛውም የመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ የመስራት ነጻነት ስለነበረው የእርሻ ሚኒስቴር አስተምሬሀለሁ በሚል ምንም ተጽእኖ አላደረገብኝም።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤትም ወዲያውኑ ስለተቀበለኝ በክቡር ከንቲባው አማካኝነት ግርማዊ ጃንሆይ ፊት ከቀረብኩ በኋላ በጽሕፈት ሚኒስቴር ማዘዣ እንድቀጠር ተደረገ።

እውጭ አገር ተምረው የሚመለሱ ተማሪዎች ሁሉ እግርማዊነታቸው ዘንድ የሚቀርቡበት ሁለት ምክንያት ነበሩት። አንዱ ግርማዊነታቸው የትምህርት ሚኒስቴር የበላይ ጠባቂ በመሆናቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ ከውጭ አገር ትምህርቱን አጠናቆ ለሚመጣ ምሁር ክብር ለመስጠትና ከሱም አገሪቱ ብዙ እምትጠብቅ ለመሆኑ መመሪያ እንዲሰጠው ለማድረግ ነው።

ማዘጋጃ ቤት ተቀጥሬ በመጀመሪያ የተመደብኩበት ቦታ በፖርክና መናፈሻ ክፍል ሲሆን፣ ሥራው የሚመራው በመንገድ ክፍል ዋና መሐንዲስ በኢንጂኒየር ኮሎምቦ ነበር። በዛን ወቅት የአፍሪቃ መሪዎች ወደ ኢትዮጵያ

ይመጣሉ ተብሎ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባሉ የሥራ ክፍሎች በሁሉም አቅጣጫ ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ ይራመድ ነበር። ልማቱ በብዛት ያተኮረው በመንገዶች ሥራና በቤቶች እድሳት ላይ ስለነበር የመናፈሻው ሥራም ከመንገዱ ጋር አብሮ ይከናወን ነበር።

ሥራው ሰፊ እየሆነ በመምጣቱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እራሱን የቻለ ክፍል እንዲሆን በመወሰኑ እኔ የዛ ክፍል ኃላፊ ሁኜ ተመደብኩ። ገና ባልተደራጀ የሥራ ክፍል በርካታ አጣዳፊ ሥራዎች ተግባራዊ ማድረግ ቀላል አልነበረም።

ብዙም ሳልቆይ ከቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስትያን ፊት ለፊት ካለው ድልድይ አንስቶ እስከ ታላቁ ቤተመንግሥት ድረስ ባለው መንታ መንገድ ማህል ያለውን ቦታ መናፈሻ ለማድረግ ጥናት በመንገድ ክፍል መሀንዲሶች ተጠንቶ በማለቅ ላይ ሳለ እኔ የመናፈሻ ሥራ ክፍል ኃላፊ ሁኜ በመመደቤ ጥናታቸውን እንድመለከትና አስተያየትም እንደሰጥበት ተደረገ።

ጥናቱ በመንገድ ክፍሉ ዋና መሐንዲስና በረዳታቸው በጅኦሜትራ ዳሩኛ የቀረበ ሲሆን የጥናቱም ዲዛይን ብዙ ግንብ የበዛበት፣ ዘመናዊ የመናፈሻ መርሆዎችን ጨርሶ ያላካተተ፣ በእጽዋቱም በኩል ለይስሙላ የተነደፈ ከመሆኑም በላይ የመኪና ማቆሚያውም 250 ተሽከርካሪዎችን ብቻ የሚይዝ ነበር። ከ250 መኪናዎች በላይ የመኪና ማቆሚያ ማመቻቸት እንደሚቻል ለክቡር ከንቲባው ገልጨ የተሻለ ፕላን እንዳቀርብ ጠየቅኋቸው። እሳቸውም የተዘጋጀው ፕላን ብዙ ጊዜ የፈጀ በመሆኑ ሥራው አጣዳፊ ስለሆነ ጊዜ የለንም አሉኝ። እኔም ሌት ተቀን ሠርቼ በጥቂት ቀኖች አደርሳለሁ ስላልኳቸው ፈቀዱልኝ።

አሥራ አምስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ:-

1) ለብዙ ግንብ የሚወጣውን ገንዘብ የሚአስቀር ፕላን በማውጣት፣
2) የመኪና ማቆሚያውን ከ250 ወደ 525 እንዲይዝ በማድረግ፣
3) የውስጥ መንገዶችንና የአትክልት ቦታዎችን ከነዓይነታቸው በዘመናዊ አቀማመጥ በመንደፍ ቅድመ ጥናቱን ሳቀርብ በመደሰታቸው ቶሎ ጨርሰው በማለት ፈቀዱልኝ።

አጠናቅቄ እንዳቀረብኩም ከኢጣሊያውያኖቹ መሐንዲሶች ጥናት ጋር እንዲወዳደር ለቴክኒክ ክፍሉ ዋና መሐንዲስ ተላከ። የመራጭ ኮሚቴው አባሎችም

1) ዋናው መሐንዲስ እራሳቸው ሰብሳቢ በመሆን
2) ሙሴ ለማርሻ የአርኪቴክት ክፍል ኃላፊ
3) ኢንጂንየር ከበደ አካለወለድ
4) ኢንጂንየር ኮሎምቦ (የመንገድ ክፍል ኃላፊ ከነረዳታቸው)
5) እኔ እራሴ (በአስረጅነት)

በነኢንጂንየር ኮሎምቦ የተጠናውን ቀደም ብለው ያውቁት ስለነበር በኔ ጥናት ላይ ብቻ እኔ እያስረዳሁ ካዳመጡ በኋላ በተለይ በሰብሳቢው መሐንዲስ ብዙ

ጥያቄ የቀረበልኝ ቢሆንም ጥያቄው ከአንድ ባለሙያ የማይጠበቅ ስህተት የሞላበት ነበር። እሱም ሁኖ በውጭ ባለሙያዎች ከተጠናው የኔ የተሻለ ሁኖ በመመረጡ ጥናቱ በክቡር ከንቲባው አቅራቢነት ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀርቦ ከጸደቀ በኋላ ሥራ ላይ ዋለ።

ወጣት ኢትዮጵያውያን ለዚህ ደረጃ በመብቃታችን ሳይሆን አይቀርም ግርማዊነታቸው የነበራቸው ደስታ ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር። ለሥራው ተቆጣጣሪነት የተመደብኩት እኔ ስለነበርኩ ውጤቱ ያማረ ሁኖ በመጠናቀቁ የአፍሪካ መሪዎች የመታሰቢያ ዛፎች መትከያ ቦታ እንዲሆን ሊመረጥ በቅቷል። ከመንገዶቹ ጋር የተቀናበረ ዘመናዊ የሆነ ለየት ያለ አቀማመጥ የነበረው መናፈሻ ነበር። የዚህ መናፈሻ ጥናት ለኔ የሥራ እድል ከፋች ከመሆኑም በላይ በግርማዊነታቸውና በብዙ ሚኒስትሮች ዘንድ ታዋቂነትን ሊአስገኝልኝ ችሏል።

## *የዛፎችና የእጽዋቶች ችግር*

በዛን ዘመን በአገራችን ሥራዬ ብሎ ለጌጣጌጥ የሚውሉ ዛፎችንና የአበባ ቁጥቋጦዎችን ችግኝ በስፋት የሚአፈላ አትክልተኛ ባለመኖሩ በዓይነትም ሆነ በምንፈልገው ብዛት አገር ውስጥ ልናገኝ አልቻልንም ነበር። በተለይም እኛ የምንፈልጋቸው ዛፎች ቁመታቸው ከሁለት ሜትር በላይ የሆኑትን ስለነበር ከውጭ አገር ገዝተን ማምጣት ተገደድን።

ዋናው ምክንያት ራእያችን የአፍሪቃ መሪዎች በሚመጡበት ጊዜ ዛፎቹም ሆኑ ቁጥቋጦዎቹ ነባር ዛፎች ሁነው ውበት እንዲሰጡ ለማድረግ ነው። ስለዚህ ከሁለት ሜትር በላይ ቁመት ያላቸውን ጃካራንዳ ዛፎች ከጣልያን አገር በአውሮፕላን ተጭነው እንዲመጡ ስናደርግ እንደ ዘንባባ፣ ችብሀና ወሽመላ ያሉትንና ሌሎች ቁጥቋጦዎችን ከአገራችን (ከአስመራና ከሐረርጌ) በካሚዎን አስጭኜ አመጣሁ።



እንዲሁም ሆለታ ወስጥ የደን ክፍል የምርምር ጣቢያ የተለያዩ የአገር ዝርያና የውጭ አገር ዛፎች ለምርምር ከ15 ዓመት በፊት ተክሏቸው ከነበረው ውስጥ ለመናፈሻ ቦታ የሚጠቅሙኝን እንድወስድ ጠይቂ ስለፈቀዱልኝ እራሴ በጥንቃቄ ከ15 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸውን ትልልቅ ዛሮች አስነቅዬ በማምጣት ቦታዎቹን አዘጋጅቼ ተከልን፡፡

በአገራችን ከሁለት ሜትር በላይ ቁመት ያለው ችግኝም ሆነ ዛፍ ተነቅሎ ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር የተለመደ ስላልነበር ዛፎቹን አምጥተን ስንተክል ያዩ ሰዎች የልጆች ጨዋታ ነው ይሉን ነበር፡፡ በሥራዬ ውጤት ሙሉ እምነት ስለነበረኝ ሳልደናገጥና ሳላመነታ ሥራዬን በጥንቃቄ ቀጠልኩ፡፡

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ለእጽዋቶች ባላቸው ከባድ ፍቅር እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴአችንን በመከታተል በርቱ ጥሩ ይዛችኋል ይሉን ነበር፡፡ ትልልቅ ዛፎችን በምንተክልበት ጊዜም ከምንም በላይ ያሳሰባቸው በመሆኑ ሌላውን ሥራችንን ካደነቁ በኋላ በማያስደነግጥ አነጋገር እነዚህ ትልልቆቹ ዛፎች የሚይዙልህ ይመስልሀል በማለት ነበር የጠየቁኝ፡፡ እኔም «አዎ ይይዛሉ ግርማዊ ሆይ» ብዬ መለስኩላቸው፡፡ በየቀኑ ከኢዮቤልዩ (ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመንግሥት) ወደ ታላቁ ቤተመንግሥት ሲሄዱ ሁኔታውን ይከታተሉ ስለነበር የወየበው ቅጠል እየወዛና አረንጓዴ እየሆነ ሲሄድ ካዩ በኋላ ከሥራ ቦታ ወደ ቤተመንግሥት አስጠርተው ድካምህ ፍሬ ያስገኘ ይመስላል ዛፎችህ ወዛቸውን እያገኙ ነው በርታ ካሉኝ በኋላ አንዳንድ ቦታዎችን በመጥቀስ ለነሱ ምን አስበሐል በማለት ጠይቀውኝ ነበር፡፡

ግርማዊነታቸው ሰው ትንሽ ነው ተብሎ አይናቅም ይሉ ነበር ለሚባለው ያገኘ ኋቸውን ማረጋገጫዎች ብጠቅስ እወዳለሁ፡፡ እኔ ገና ተራ ሠራተኛ የሆንኩ በዝቅተኛ ሥራ ላይ ያለሁትን የሥራ እንቅስቃሴ በመውደድ እመንገድ ላይ መኪና አቁመው ስለሥራው ውጤት ማመስገን በርታ እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው መመረቅ የተለመደ ጠባያቸው ሁኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ ጥሩ የሠሩ ወጣቶችም ይህን ይመሰክራሉ፡፡ ከሥራ ቦታ ተጠርቼ የሥራ ልብስ ለብሼ ወደ ቤተ መንግሥት በመግባቴ ይቅርታ ስጠይቅ የሰጡኝ መልስ ይህን ካንተ አንጠብቅም በሥራህ ላይ ብቻ በርታ በዚሁ ቀጥል የሚል ነበር፡፡ ወደ አሁኑ ዘመን መለስ ልበልና የተያዘው ዘዴ ባለው ላይ መገንባት ሳይሆን የታሪክ ማስረጃዎቻችንን አፍርሶ ሌላ መካብ ነው፡፡ መሆን የነበረበት ያለፈውን ስልጣኔ ሂደት ሳያጠፉ በአዲስ ቦታ ላይ መገንባቱ በጣም አስፈላጊ ሲሆን ከ47 ዓመት በፊት የነበረውን መናፈሻ አፍርሶ በላዩ ላይ አዲስ መገንባት ታሪክን እንደማውደም ነው የምቆጥረው፡፡ ግንባታው ሌላ ቦታ ቢሆን ኖሮ ከተማዋን በልማት ያሰፋት ነበር በሚል አስተያየቴ አልፈዋለሁ፡፡

## የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (E.C.A) ሕንፃ ጥናት

በዚያን ወቅት ዋናውና ትልቁ የፕሮጀክት ጥናት የአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኮሚሽን ሕንፃ ጥናት ነበር፡፡ የአፍሪካ መሪዎች ሲመጡ ስብስባ የሚአደርጉት በዚህ ሊሠራ በታቀደው ሕንፃ ውስጥ ስለነበር ባማረና በተፋጠነ ሁኔታ ሥራው ተጠናቆ እንዲያልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ነበር፡፡

ፕሮጀክቱ ይዘጋጅ የነበረው በታዋቂው አርኪቴክት ሜዜዴሚ ሲሆን ጥናቱ አልቆ ለግምገማ መቅረብ ላይ ስለደረሰ ገምጋሚ ባለሞያዎች ሲመረጡ እኔም በሳይት ፕላነርነት እንድሳተፍ በአርኪቴክት ክፍል ሀላፊው በሙሴ ለማርሻ በኩል ጥሪው ደረሰኝ፡፡

ከስብሰባው በፊት ቦታውን በመጐብኘት ከጥናቱ ጋር ማገናዘብ ስለነበረብኝ ጊዜ በመውሰድ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ አጠናሁ፡፡ በስብሰባውም ቀን ተገኝቼ አንጋፋ የሆኑት ባለሞያዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሰጡትን አስተያየት በጥሞና አዳመጥኩ፡፡ ቀጥሎም በሙሉ ልብ እዚህ ጥናት ላይ ሁለት ከባድ ስህተቶች አሉ እነሱም የግድ መስተካከል አለባቸው ስል ለአስተያየቴ ብዙም ትኩረት አልሰጡትም ነበር፡፡

አስተያየቴን በመቀጠል፡-

1ኛ/ የሕንፃው ሰፊውና ዋናው ገጽታ ወደ ሰሜን (ወደ ሒልተን ሆቴል) በመሆኑ መታየት የሚገባው የሕንፃው ውበት ተደብቋል፡፡ ዋናው ገጽታ ወደ ዋናው መንገድ መዞር አለበት፡፡

2ኛ/ ፊት ለፊቱ ወደ ዋናው መንገድ ቢሆን እቢሮው ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ሠፊውንና ውብ የሆነውን የከተማ ክፍል በማየት እንዲሁም መንገደኛው የሕንፃውን ገጽታ በመመልከት የመደሰት እድል ይሰጣቸዋል፡፡

3ኛ/ ሰፊው የሕንፃው ክፍል ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ በመሆኑ በሰሜን በኩል ያሉት ቢሮዎች አመቱን ሙሉ ፀሐይ ስለማያገኙ እንዲሁም በደቡብ በኩል ያለው ሰፊ ገጽታ ፀሐይ የሚአገኘው መሐል ቀን ላይ ለሶስት ሰዓት ያህል ብቻ በመሆኑ ባጠቃላይ እዚህ ሕንፃ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች በማቀዝቀዣ ውስጥ ሁነው እንዲሠሩ የተፈረደባቸው ይመስላል፡፡ የሕንፃው ዋናው ፊት ወይም ገጽታው ወደ ዋናው መንገድ ቢዞር ውበትም አግኝቶ በስተኋላው የምስራቅን ፀሀይ በሙሉ ስለሚአገኙ ከማቀዝቀዣ ውስጥ ወጡ ማለት ነው በሚል አሳሰብኩ፡፡

ከዚህ በኋላ አርኪቴክት ሜዜዴሚ ነበሩ የተናገሩት፡፡ በአርኪቴክት ጌታቸው የቀረበው አስተያየት ልክ ነው አሻሽዬ አቀርባለሁ ስላሉ ሁሉም ተስማሙ፡፡ በቀጣዩ ጊዜ ፊቱን ወደምዕራብ አዙረው ለውበቱም ፏፏቴ ጨምረው አሳምረው አቀረቡት፡፡ ሕንፃው አሁን ባለው መልክ ባይሰራ ኖሮ የምንግዜውም ጸጸት ይሆን ነበር፡፡ በዛን ወቅት ከመደበኛ ሥራዬ ውጭ በሌላ ሥራዎችም ጣልቃ በመግባት እሳተፍ ስለ ነበር የሥራ ውጤቱ በብዙ በኩል ጠቅሞኛል፡፡ ለምሳሌ አንድ ግዜ ለአንድ አስቸኳይ ሥራ ጨረታ ሲወጣ ተቋራጮች ከ 18,000 ብር በታች አንሠራም ብለው ድርቅ አሉ፡፡ በጊዜው ይህ አሀዝ እጅግ ብዙ ገንዘብ ነበር፡፡ ሥራው በአጣዳፊ መሠራት ስለነበረበትና መቅረትም ስለማይችል መወሰኑ ከባድ ነበር፡፡

ስለሥራው ውይይት ሲደረግ ባጋጣሚ እኔ እቦታው ላይ ነበርኩ፡፡ ጣልቃ ገብቼ ለክቡር ከንቲባው እኔ ልሥራው፤ የውሀ ቧንቧዎችን በመገጣጠም መሥራት ይቻላል፤ ማዘጋጃ ቤት የውሃ ክፍል ቧምቧና ሠራተኛ በውሰት ይስጠኝ፤

*የመንገድ ክፍልም የመንገድ መከለያ ገመድ ያውሰኝ፤ አንዳንድ እቃዎችን ለመግዣ **3000** (ሶስት ሺህ) ብር ቢሰጠኝ በዚህ መልክ እሠራዋለሁ በሚል አስረዳሁና ተስማሙበት፡፡*

*የጠየቅሁት ሁሉ ተሰጠኝና ሥራውን ጀመርኩ፡፡ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወደማጠናቀቁ ተቃረብሁ፡፡ ሥራው ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ከንቲባው እቦታው ላይ ይገኙ ነበር፡፡ በሥራው ውጤት በመርካታቸው አብረዋቸው ቆመው የነበሩትን የሂሣብ ክፍል ምክትል ሹም የአቶ ጌታቸው ደመወዝ ስንት ነው ብለው ጠየቁ፡፡ ምክትል ሹሙም የምስክር ወረቀታቸው ከምዕራብ ጀርመን ስለሆነ የደረጃ ማረጋገጫ ከትምህርት ሚኒስቴር እየጠየቅን ነው አሉ፡፡ ክቡር ከንቲባውም ከዛሬ ጀምሮ ሰባት መቶ ብር እንዲከፈለው ብለው አዘዙ፡፡ ለዛ ጊዜ ብዙ ገንዘብ ነበር፡፡*

*ዋናው የሂሳብ ሹም አቶ ዮሴፍ አስቤ የሚባሉ ጠንቃቃና ጠንካራ ሠራተኛ ነበሩ፡፡ ይህ የጭማሪ ትእዛዝ ሲደርሳቸው ይገባዋል እሱ ከመጣ ነው እነኢንጂኒየር ኮሎምቦ ወምበራቸው ላይ ቁጭ ብለው መሥራት የጀመሩት በሚል ተችተዋል፡፡*

*ክቡር ከንቲባው ከፍተኛ ምሁር ስለሆኑ የተማሩ ወጣቶችን ማዘጋጃ ቤት ውስጥ በብዛት የቀጠሩና አሠራራችንንም በቅርቡ ሁነው የሚከታተሉ ሠርተው የሚአሠሩ አለቃ ነበሩ፡፡ በእኔ አሠራርም ላይ እምነት ስላደረባቸው የሥራ ጊዜን እንዳናጠፋ ሁኔታውን በዝርዝር ካስረዳሁኝ በኋላ የተስማማንበትን (እምፈርምበትን) በጽሁፍ አዘጋጅተህ አቅርብልኝ ይሉኛል፡፡ ይህ አባባላቸው የበለጠ ተጠንቅቄ እንድሠራና ኃላፊነትም ስለጣሉብኝ ረጋ ብዬ እንድሠራ መመሪያ ሆነኝ፡፡*

## *ተጨማሪ የሥራ ክፍሎች*

*የሥራ ክፍላችን በየጊዜው ባሳየው የተሻለ የሥራ እንቅስቃሴና መልካም የሥራ ውጤት የተነሳ ሌሎችንም የሥራ ክፍሎች ደርበን እንድንሠራ ተደረገ፡፡ እነዚህም የሥራ ክፍሎች የመንገድ ጥገናና የጽዳትና የጤና ጥበቃ ነበሩ፡፡ ዝውውሩ ብዙ ምክንያቶች ነበሩት፡፡ የክፍሉ ሠራተኞች በአንድ ቦታ በመቆየታቸውና በአንድ ዓይነት የአሠራር ዘዴ ይሠሩ ስለነበር በመሰላቸትና እርስ በርስ በመላመድ ዲሲፒሊን ጭምር ጠፍቶ ዋልጌነት ሰፍኖ ነበር፡፡*

*ጥሩውን በመጠበቅ በጉደለው ቦታ አቅም በሚፈቅደው መሠረት ዘመናዊ አሠራርን መተካት ጀመርን፡፡ ለምሳሌ ዋና ዋና መንገዶች ላይ አልፎ አልፎ ተቆፍረው የሚገኙትን ጉድጓዶች ትራፊክ በማይበዛበት ሰዓት ማታ እየተዘዋወረ የሚደፍን ጠጋኝ ቡድን አቋቋምን፡፡*

*የዝናብ ውሃ በመንገድ ላይ እየተጠራቀመ አላፊ መኪና እግረኛው ላይ እየረጨ በማስቸገሩ ፍሳሽ መቀበያ ቱቦዎች ባለማቋረጥ እንዲጠረጉ አረግን፡፡ የግር መንገዶች ለእግረኛው ምቹ ስላልነበሩ እግረኛው ለመኪና በተዘጋጀው መንገድ ላይ በመሄድ አደጋ ላይ ስለወደቀ ለግር መንገዱ ትኩረት ሰጠን፡፡*

በጽዳትና ጤና ጥበቃው ክፍልም ከባዱ ችግር የቆሻሻ ማስወገዱና ከየመጸዳጃ ክፍል የሚወጡ ፍሳሾችን መቆጣጠር ነበር፡፡ የሚከተሉትን የማሻሻያ እርምጃዎች ወሰድን፡፡

1) በርካታ ቆሻሻ ይጣልበት በነበረው ቦታ ላይ እነኝህ አሁን በየቦታው ተቀምጠው የሚገኙትን ዓይነት ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ከኦርቢስ ኩባንያ በሐይድሮሊክ እያነሳ ከሚአንጉዘው መኪና ጋር በክሬዲት በመግዛት በየቦታው አስቀመጥን፡፡ ገንዳዎቹ መንገድ ላይ ቆሻሻ እንዳይበትኑ ክዳን ነበራቸው፡፡

2) ማንኛውም የግል መኖሪያ ባለቤት የቤቱን ቆሻሻ የሚጥልበት የዝምብ መከላከያ ክዳን ያለው ማጠራቀሚያ በግሉ እግቢው ውስጥ አዘጋጅቶ የጽዳት መኪና መምጣቱን የሚያመለክት ልዩ ጥሩምባ ሲነፉ አውጥቶ እንዲገለብጥ ተደረገ፡፡ ከዚህ ውጭ እመንገድ ላይ ሲያፈስ ቢገኝ በጽዳት ዘበኞች ተይዞ ይቀጣ ነበር፡፡ እንዲሁም በአቅራቢያው በተቀመጠ ገንዳ ውስጥም መገልበጥ ይችላል፡፡ ከሞላ ጎደል ውጭ ማፍሰስ አይፈቀድም ነበር፡፡ የሽንት ቤት ፍሳሽ እራሱ ግቢ ውስጥ እንዲሆን እንጅ ወደ መንገድ እንዳይሆን ተደረገ፡፡ ከግቢው ውጭ ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ቢገኝ ወዲያውኑ በመጣጭ መኪና እንዲያስመጥጥ ይገደዳል፡፡ ግዴታውን ባያሟላ ቅጣቱ ከፍ ያለ ነበር፡፡ ጉረቤትም ሆነ የጽዳት ዘበኞች ተባብረው የማስፈጸም መብት ነበራቸው፡፡

ያልተመረመረ ከብት በየመንደሩ እንዳይታረድ መቆጣጠሩና ሕጉን ማስከበሩ እጅግ አዳጋች ነበር፡፡ ወደ ቄራ ወስደው ማሳረድ ስላልተለመደ ከነበረው ባሕላችን እስከምንላቀቅ በልኳንዳ ደረጃ ሥጋ የሚሸጡ ሁሉ በቄራ እንዲያሳርዱና ከዚያ ውጭ በጓሮአቸው ያልተመረመረ ከብት አርደው ቢገኙ ሥጋው ተወርሶ እንዲጣል ተደረገ፡፡ ግለሰቦቹም በተቻለ መጠን የተመረመሩ ከብቶችን ገዝተው እንዲያርዱ ከፍተኛ ምክር ይሰጥ ነበር፡፡ ሌላው በጣም አሳሳቢ የነበረው ከውጭ አገር ታሽገው የሚመጡ ምግብ ነክ ነገሮች ሲገቡም ሆነ አገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ጥቅም ላይ የማዋያ ጊዜአቸው ማለፉን የሚቆጣጠሩ ተቋሞች ስላልነበሩ ለዚሁ ሥራ የሠለጠኑ ሳኒቴሪያኖችን በያንዳንዱ የጤና ጣቢያ ውስጥ ተመድበው እንዲሠሩ ተደረገ፡፡ ከሞላ ጉደል የሱቆችንም ጽዳት ለመቆጣጠር ተሞክሯል፡፡

በስፋት አይሁን እንጂ የሰለጠኑ አገሮች ይጠቀሙበት የነበረውን ዓይነት አሠራር ያልጀመርንበት የሥራ ክፍል አልነበረም፡፡ ችግሩ ሥራውን በስፋት የሚአስፈጽም የተማረና የሰለጠነ በቂ ሠራተኛ አለመገኘቱ ነበር፡፡

የነዋሪውም ሕዝብ በሙሉ አለመሰልጠን ችግሩን ያባብሰው እንደነበር ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ከኛም ከሠራተኞቹ ውስጥ ትእዛዝ የማይቀበል፤ ጠጥቶ ሥራ ላይ የሚመጣ፣ የሥራ ሰአት የማያከብርና ሰነፍ ሰራተኛ መኖሩ አይካድም፡፡

እነዚህ የሥራ ክፍሎች በአዲስ መልክና በአዲስ የሥራ ኃላፊ እንዲመሩ በመደረጉ ሠራተኛው ዘመኑን በተከተለ የአሠራር ዘዴ መስራት ስለተገደደ በሠራተኛው ላይ ብዙ የሥነ ምግባር (የዲሲፒሊን) ለውጥ ይታይ ነበር፡፡

አልፎ ተርፎም አንዳንድ ሰራተኞች ከሌሎች ክፍሎች በስነምግባር እንዲታነጹ ወደኛ ክፍል በመላካቸው ክፍላችን ጠባይ ማረሚያ ሳይሆን የሥራ ክፍል ስለሆነ ከዛሬ ጀምሮ ጠባየ ብልሹ ሰዎች ወደኛ እንዳይላኩ የማለት ማሳሰቢያ ለአስተዳደር እስከመጻፍ ደርሰን ነበር፡፡

## *የካርታና ቶፖግራፊ ክፍል*

ይህ የሥራ ክፍል ይመራ የነበረው ፕሮፌሰር ጉላቲ በሚባሉ የሕንድ ተወላጅ ነበር፡፡ የሳቸው ምክትል ሁኜ በመሾሜ ከዚህም ክፍል መጠኑ የበዛ ጠቃሚ ልምድ እያገኘሁ ሠራሁ፡፡ በተለይም የአዲስ አበባን ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ በተለያየ ጊዜ በአየር የተነሱትን ካርታዎች (ማፖች) ማገላበጥ የግድ ነበር፡፡

ለማንኛውም የከተማ ልማት ጥናት መሠረታዊ መነሻ የሚሆኑት የመንገድ አውታሮች፣ ገደልና ሜዳውን፣ ወንዙንና ሸንተረሩን፣ ሕንፃ የሰፈረበትንና ባዶውን ቦታ ሌሎችንም ለከተማ ዝርዝር ጥናት የሚጠቅሙ መረጃዎችን እንድገነዘብ አስችሎኛል፡፡

## *ወደ አዲስ አበባ የፕላን ክፍል ዝውውር*

ሰኔ 12 ቀን 1955 ዓ.ም ወደ ፕላን ክፍል ተዛወርኩ፡፡ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትዕዛዝ መሆኑንም የዝውውሩ ደብዳቤ ያስረዳ ነበር፡፡ የቤት ሥራ ፈቃድ ክፍልም በዚሁ ሥር የነበረ ሲሆን የፓርክና መናፈሻ ክፍልም በዚሁ ሥር ተመድቦ ነበር፡፡

ወቅቱ የውጭ ኤክስፐርቶች በሙሉ ለቀው የመሥሪያ ቤቱ ቴክኒካዊ ክፍሎች በኢትዮጵያውያኖች መካሄድ የጀመሩበት ጊዜ ነበር፡፡ ሥራውን እንደተረከብኩ የነበረውን አሠራር አንድ በአንድ ከተመለከትኩ በኋላ ጥሩውን አሠራር መሠረት በማድረግ መሻሻል በሚአስፈልጋቸው ላይ ለውጥ ማድረግ ጀመርኩ፡፡

እነዚህም የተደረጉ ማሻሻያዎች፡-

1ኛ. ሥራዎቹን በሥራ ጠባያቸው ለየሁ፡፡

2ኛ. ለየሥራውም ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣት ይችላሉ ያልኳቸውንና ታማኝ ናቸው ያልኳቸውን ባለሙያዎች ለይቼ መደብኩ፡፡

3ኛ. ለያንዳንዱ ሠራተኛ (እስከ ተላላኪ ድረስ) ሥራውንና ኃላፊነቱን የሚአስረዳ መመሪያ አስወጥቼ አደልኩ፡፡

4ኛ. አንዱ በሌላው ሥራ እየገባ ለሚፈጠረው ስህተት ተጠያቂ በመጥፋቱ ይህ ሁኔታ እንዳይደገም አደረግሁ፡፡

5ኛ. ማንኛውም ሠራተኛ (እኔን ጨምሮ) በየቀኑ የሚመጣውን ባለጉዳይ አስተናግዶ ከመጨረሱ በፊት ውዝፍ ሥራውን እንዳይሠራ አደረግሁ፡፡

6ኛ. ቀደም ብሎ ተጠራቅሞ ለነበረው ሥራ ልዩ አጣሪ ሠራተኞች መደብሁ፡፡

የኔ ቅድሚያ ሥራ የነበረው መሠራት ያለባቸውን ሥራዎች መንደፍና ለነሱም ቅደም ተከተል የሥራ ጊዜ ማውጣት ነበር።

አንድ ሚሊዮን ተኩል ሕዝብ ከሚኖርበት ከተማ በየቀኑ የሚጐርፈውን ጥያቄ በአንድ ቢሮ ማስተናገዱ እጅግ ከባድ ነበር። በተለይም ቤት የሚሠሩ፣ ካርታ የሚአወጡ፣ መሬት የሚገዙ ግለሰቦች የፕላን ክፍልን ማረጋገጫ ስለሚፈልጉ ዝርዝር ጥናት ባልወጣለት ከተማ የመንገዱን አቅጣጫና ስፋት፣ ምን ዓይነት ሕንፃ እንደሚሠሩ፣ ባጠቃላይ አዲስ ፕሮጀክት የማይነካው ለመሆኑ ዘለቄታ ያለው ማረጋገጫ መስጠቱ አዳጋች ነበር።

ስለዚህ ለማስተር ፕላን ክፍል የራሱን የሥራ ቅደም ተከተል አወጣን። ይኸውም፣

1ኛ. ልማት በፍጥነት በሚንቀሳቀስባቸው ክፍሎች የኘሮጀክት መንገዶችን አሁን ቢሠሩም ባይሠሩም አቅጣጫቸውን ነድፎና ስፋታቸውንም ወስኖ ማስቀመጥና፤

2ኛ. በየጊዜው ለሚመጡ ባለጉዳዮች መልስ ለመስጠት እንዲቻል ለየዞኑ የተመደቡት ቴክኒሽያኖች ቦታውን ካዩ በኋላ ጥናት ያልተደረገለት ቦታ መሆኑ ከተረጋገጠ ወዲያውኑ ለማስተር ፕላን ክፍል ተላልፎ ቅድሚያ በመስጠት ዝርዝር ጥናት መጀመር ነበር።

በተጠቀሱት ነጥቦች መሠረት ሥራችንን ስለጀመርን ባለጉዳዮችም በተረጋገጠ ፕላን ጉዳያቸው እንዲያልቅላቸው ጊዜ በመስጠት ስለተባበሩን ሥራችን ቀና እየሆነ መጣ።

ችግሩ የሚበዛው ሰፋፊ መሬት ያላቸው ግለሰቦች መሬታቸውን በሚሸጡበት ጊዜ መንገድ የማያልፍበት መሆኑና መንግሥት ለሌላ አገልግሎት ያልመደበው መሆኑ እንዲረጋገጥላቸው አጥብቀው ስለሚጠይቁ በቅድሚያ ሰፋፊ ቦታዎች ላይ ዝርዝርና ሌላም ጥናቶችን ማድረግ ነበረብን። አሠራሩ የላንድስኬኘ አርኪቴክት ሞያን ስለሚጠይቅ እኔም ከሌሎቹ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ለዓይነት የተወሰኑ ፕሮጀክቶችን አብሬ ሠራሁ። ለምሳሌ:- በጃፓን ኤምባሲ ጀርባ ያለውን አካባቢ፣ ከአዲሱ አየር ማረፊያ ድልድይ አንስቶ ወንዙን በመከተል እስከ ኦሜጓድ ቢሮ አካባቢ ያለውን ቦታ፣ እንዲሁም አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ አጠገብ ካለው ከቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ያለውን ቦታ በሙሉና ከቫቲካን ኤምባሲ ድልድይ አንስቶ ወደ ምዕራብ ዳገቱ ላይ ያሉ ቦታዎችን በሙሉ አጠናን።

የዝርዝር ጥናት ሥራ መጀመሩ ሌላም ከባድ ችግሮችን አቃሏል። ለምሳሌ:- የመንገድ ክፍል መንገድ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ መብራት ኃይል፣ ቴሌኮሙኒኬሽንና የውሃ ክፍል የየራሳቸውን ሥራ ለማከናወን ሲሉ በተለያየ ጊዜና በተለያየ ቦታ መንገዶቹን ይቆፍራሉ። የመንገድ ክፍልም የተቀበሩ የስልክና የውሃ ባንቧዎችን ይበጣጥሳል። እነዚህም በጥናት ያልተባበሩ ሥራዎች በሚያደርሱት ጥፋት የአገር ኤኮኖሚ ይጐዳል።

እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ በሕብረት መሥራት ጠቃሚ ስለሆነ የዝርዝር ጥናቱ ንድፍ እንደተጠናቀቀ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን መሥሪያ ቤቶች ባለሞያዎች በጥናቱ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አደረግን። የትራፊክ ጽ/ቤትም ጉዳዩ ስለሚመለከተው ተሳታፊ ነበር። የወደፊት ትንቢታዊ እቅዳችንን ነዋሪው ሕዝብ አውቆ እንዲተባበረን በጋዜጣና በሬዲዮ ማስገንዘብ ጀምረን ነበር። እነዚህን ዝርዝር ጥናቶች በምናከናውንበት ወቅት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማዘጋጃ ቤቱን ይጐበኙ ስለነበር በኛ ጅምር ስራዎች በመደሰታቸው በተከታታይ በጥቂት ወራቶች ውስጥ ደጋግመው እየመጡ በመጐብኘት ያበረታቱን ነበር። እኔ ወደ ፕላን ክፍል እንድዛወር የሆነውም በግርማዊነታቸው ቀጥተኛ ትዕዛዝ ለመሆኑ የዝውውር ደብዳቤው ይገልጻል። ከበጐ ቅናት የተነሳ ሌሎቹ የሥራ ክፍሎች በተደጋጋሚ ባለመጐብኘታቸው ጃንሆይ የኛን ክፍል የእንጀራ ልጅ አደረጉት ይሉ ነበር።

## *ከህንጻ ኮሌጅ ጋር የነበረን ግንኙነት*

የህንጻ ኮሌጅ ፕሮፌሰር የነበሩት ዶክተር ሥዩም ተማሪዎቻቸውን ለማስጐብኘት ፈቃድ ጠይቀው በርካታ ተማሪዎችን ይዘው መጥተው አሠራራችንን አይተው ነበር። ከጐብኝታቸው በኋላም ባደረጉት ንግግር «እኛ ማዘጋጃ ቤት እንዲህ ዓይነት አስገራሚ ሥራ ይሠራል ብለን አላሰብንም» ካሉ በኋላ ለተማሪዎቻቸው ደግሞ «ከዚህ ቤት ብዙ እንደምትማሩ አምናለሁ።» ብለው ተሰናበቱን። ከዛ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት ተማሪዎቻቸውን አምጥተዋል።



*እኛም ተማሪዎቻቸው እውነት ባልሆኑ ፕላኖች ላይ ልምምድ ከሚያደርጉ ይልቅ ዝርዝር ጥናት ከምናደርግባቸው ቦታዎች ላይ ብንልክላቸውና ተማሪዎቹ ልምምድ ካደረጉበት በኋላ የመምህራኑ እርማት ተደርጐበት ይመለስ በሚል ተስማምተን ያጠኑዋቸውን ጥናቶች ለኛም እንደ አማራጭ የተጠቀምንበት ጊዜ ነበር። ካልተጠበቀ ሰው ጥሩ ሐሳብ ሊመነጭ ስለሚችል የሐሳብ መለዋወጥም እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ ዶ/ር ሥዩምን ለምክራቸውና ከኮሌጁ ጋር ለፈጠሩልን ግንኙነት በየጊዜው እናመሰግናቸው ነበር።*

*ኮሌጁ ለኮንስትራክሽን የሚውሉትን የግንባታ እቃዎች ጥራትና ጥንካሬ የሚያረጋግጥ ክፍል ስለነበረው፣ የምርምር ውጤታቸውንም ስለሚልኩልን የቤት ሥራ ፈቃድ ክፍል አንዱና ዋናው ተጠቃሚ ክፍል ነበር።*

## *የማስተር ፕላን ክለሳ ለምን አስፈለገ?*

*ጣልያኖች ከለቀቁ በኋላ፣ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያው ማስተር ፕላን የተዘጋጀው **900,000** የሚሆንን ሕዝብ ታሳቢ አድርጐ ለሱ መኖሪያም እንዲኖረው ቦታ ለማመቻቸት ነበር። ከአካባቢው የሚገኘው የመጠጥ ውሃ፣ ምግብና ማገዶ (እና ሌሎችም) አቅርቦቶች ለከተማው ነዋሪዎች የሚፈልጉትን አሟልቶ ጥሩ ኑሮ እንዲኖሩ ያደርጋል በሚል መነሻ ሀሳብ ነበር የመጀመሪያው ማስተር ፕላን የተዘጋጀው። ጥቂት ጊዜ ሳይቆይ የህዝቡ ብዛት በመጨመሩ የከተማው የቆዳ ስፋት ወይም ክልል እንዲጨምር ከአንዱም ሁለቴ ለፖርላማ ሀሳብ እየቀረበ ፀደቀ።*

*በእነዚህ አዲስ በክልሉ ውስጥ ለገቡትና ለበፊቶቹም የከተማ ክልሎች የሚያገለግል የማስተር ፕላን ክለሳ ማስፈለጉን ስላመንኩበት በተለያዩ ጊዜአቶች በተለያዩ የድርጅቱ ባለሙያዎች የተደረጉትን ክለሳ መሠረት ሳልለቅ ከ **1956** ዓ.ም እስከ **1965** ዓ.ም የሚያገለግል የ**10** ዓመት ፕላን ክለሳ በግሌ አዘጋጀሁ። ይህም ክለሳ በአብዛኛው ያተኮረው አሁን በቅርቡ ተጠናቆ ሥራ ላይ የዋለውን የቀለበት መንገድና በከተማው ውስጥ ከፊሉ ተሠርቶ ገና ያልተሠሩትን ዋና ዋና መንገዶች ንድፈ ሀሳብ ማካተቱ ላይ ሲሆን ክለሳው የመሐል ከተማውንም ከፒያሳ ወደ ብሔራዊ ባንክ ያዛወረ ጥናት ነበር።*

*እነዚህ ከአንዱ ከተማ ጫፍ ወደ ሌላውና ወደ ቀለበቱ መንገድ የሚአገናኙት ሰፋፊ መንገዶች በዛን ጊዜ ተነድፈው በማስተር ኘላኑ ውስጥ ባይካተቱ ኖሮ የአሁኑን የመኪና ብዛት ማስተናገድ የሚችሉ መንገዶች አይኖሩም ነበር። አሁንም ቢሆን በሕዝቡ መጠን የለሽ መጨመርና የመኪና ብዛት የተነሳ የወደፊት ችግራችን ቀላል አይሆንም። እንዲሁም የክለሳው የፕሮጀክት ንድፍ ቀደም ብሎ ባይሠራና ሕንፃዎችና ኢንዱስትሪዎች ለመንገድ ቅየሳ አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ ተሠርተው ቢሆን ኖሮ አዲስ መንገዶችን ለመክፈት ሲባል ስንት ቤቶችና ኢንዱስትሪዎች በፈረሱ ነበር። የአገሪቱን ኤኮኖሚም ከመጠን በላይ እንደሚጐዳውና ግለሰቦቹንም ለከፍተኛ ኪሣራና የሞራል ውድቀት እንደሚዳርጋቸው አስረጂ አያስፈልግም። በዛን ዘመን የነበሩን ዘመናዊ እቅዶች በርካታ ሲሆኑ ከ**30** ዓመት በኋላም (አሁንም) ገና ተፈጻሚ አልሆኑም።*

*ለመንገዶች ጥናት መሠረት ያደረግሁት በመጨረሻ ጊዜ በአየር የተነሳውን ካርታ ነበር። በርካታ ንብረት ያልሰፈረባቸው መሬቶች ላይ የአስፋልትና ጥርጊያ መንገዶችን እንዲሁም የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን በማስፋትና አንዱን ከሌላው ጋር በስነሥርዓት በማገናኘት ከነደፍኩ በኋላ ቦታዎቹን ደጋግሜ በመጐብኘት መሻሻል አለባቸው የምንላቸውን በማስተካከል በክለሳ ደረጃ ነድፌ ያዝኩ።*

*ቀጥዬ የቀለበት መንገዱን ከነደፍኩ በኋላ ሁሉንም ዋና ዋና መንገዶች ከቀለበት መንገዱ ጋር አያያዝኩ። በስተሰሜን በኩል ሊኖር የሚገባውን የቀለበት መንገድ ግን በሐሳብ ደረጃ እንጂ ከደሴ መንገድ እስከ ጐጃም መንገድ ያለውን በንድፍ አላስቀመጥኩም፤ ምክንያቱም ከእንግሊዝ ኤምባሴ፣ ከመስኮብ ኤምባሲና ከጀርመን ኤምባሲ ጀርባ ዳገቱን ተከትሎ መቀየሱ ትንሽ ስላጠራጠረኝ ነበር። ሌሎች አማራጮች ስለነበሩ ነው የተውኩት። ነድፌ የጨረስኳቸውን መንገዶች በሙሉ በዋናው ማስተር ፕላን ውስጥ እንዲገቡ ካደረግሁ በኋላ፡-*

1) *የከተማ ውስጥ ዋና ዋና መንገዶችን፣*
2) *የቀለበት መንገዶችን፣*
3) *መሐል ከተማውን ወደ ብሔራዊ ቲያትር ያዛወረውን፣*
4) *የባንቲቀጡና የቁርጡሜን ወንዞች በአካባቢው በሚሠሩ ሕንፃዎች ተሸፍነው በሥር እንዲያልፉ የታቀደውን፣*
5) *ዋናው የባቡር ጣቢያና መጋዘኖች ከቀለበት መንገድ ጠርዝ ተነስተው እስከ ኮሎናልፒ ባለው ቦታ ላይ እንዲሰፍሩ የሚአደርገውን ፕላን የ10 ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ የማስተር ፕላን ክለሳ ፕላን ላይ አሰፈርኩ።*

*ለባቡሩ ጣቢያ መዛወር ዋናዎቹ ምክንያቶች፡-*

1) *ለጣቢያው መስፋፊያ ለምሳሌ፣ ለፉርጐዎች ማቆሚያ፣ ለጋራዥ፣ ከውጭ አገር ለሚመጡ የንግድ እቃዎች ማሳረፊያ መጋዘን መሥሪያ፣ መኪናዎች ማራገፊያ፣ እንዲሁም ከአገር ውስጥ ለኤክስፖርት ተብለው ከክፍለ ሀገሮች ለሚመጡ እቃዎች ማሳረፊያ የሚበቃ ባዶ ቦታ በመሐል ከተማ ውስጥ ስለማይገኝ፣*
2) *ለእነዚህ የንግድ እቃዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡት ከባድ ካሚዮኖች ወደ ከተማው መሐል በመግባት መንገድ ከማጣበባቸውና የትራፊክ ችግር ከመፍጠራቸውም በተጨማሪ የከተማውን አየር በጭስ ስለሚበክሉ የባቡር ጣቢያ ወደ በከተማ ዳርቻ እንዲዛወር የሚያደርግ እቅድ ሠርቼአለሁ።*

*ይህንንም የክለሳ ጥናት በአማርኛና በእንግሊዝኛ አዘጋጅቼ በቀጥታ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቀረብኩ። ለከንቲባውም ሆነ ለሌላ ባለስልጣን በቅድሚያ ያላቀረብኩበት ዋናው ምክንያት ውሳኔ ሳያገኝ ይዘገያል ወይም ውሳኔ ያጣል ብዬ በመገመቴ ነበር። እንዳሰብኩትም ከሰጠኋቸው ከሶስት ቀን በኋላ ጃንሆይ ጠሩኝ። ለከንቲባው ሰጥተኸዋል ወይ አሉኝ። እኔም አልሰጠኋቸውም አልኩ።*

ስጠው አሉና እግዚአብሔር ይባርክህ ብለው አሰናበቱኝ፡፡ ሳይዘገይ ጥናቱ ሥራ ላይ መዋል ጀመረ፡፡

ሌላው ሀሳብ የመሀል ከተማው ከፒያሳ ወደ ብሄራዊ አካባቢ ይዛወር የሚለው ነው፡፡ለመሐል ከተማው አለመስፋፋት አስተዋጽኦ ያደረገው የአካባቢው የመሬት ባለቤቶች ከዛሬ ነገ ከፍተኛ ዋጋ ያወጣልናል በማለት በጊዜው ዋጋ ለአዲስ መጤዎች ለመሸጥ ባለመፍቀዳቸው፣ ሕዝቡ በአነስተኛ ዋጋ መሬት ለመግዛት በተቻለበት በገጠር ቦታዎች እየገዛ ቤት በመሥራቱ ሳተላይት ከተሞች በመፈጠራቸው፣ የመሃል ከተማው ቦታዎች መሸጫ ዋጋ የባሰ እየዘቀጠ በመሄድ ይባስ እንዳይከስሩ በየጊዜው ባለው የነጻ ዋጋ እየተስማሙ በመሸጥ አዳዲስ ቤቶች እንዲገነቡ ወይም በመሬታቸው ግምት ገንዘብ ካለው ሰው ጋር እየተሻረኩ ዘመናዊ ቤቶችን እንዲሠሩ ቢመከሩም እምቢ ስላሉ ልማቱን ለማጧጧፍ ሲባል መሐል ከተማውን ወደ ብሔራዊ ቲያትር ማዛወሩ ግድ ሆነ፡፡ ዘመናዊ ሕንፃዎችም ባጭር ጊዜ ውስጥ መገንባት ጀመሩ፡፡ ይህም ሆኖ መሐል ከተማው (ፒያሳ) አሁንም በቂ መሻሻል አላሳየም፡፡

በዛን ዘመን በነበረው ሕግ የግለሰብን መሬት ማንም ሰው ወይም መንግስት በትዕዛዝ ሊወስድበት ወይም ሊይዝበት አይችልም፡፡ በመሬቱ ላይ ባለርስቱ ሊገነባ ካልቻለና የልማት ጋሬጣ ከሆነ ብቻ ህጉ ለግልም ሆነ ለመንግሥት ሸጦ ቦታውን እንዲያስረክብ ያዘዋል፡፡ በተጨማሪም ለመንገድ፣ ለመንግሥት መስሪያ ቤትና ለማሕበራዊ አገልግሎት፣ ለፓርክና መናፈሻ፣ ለወንዝ ዳር ዛፍ መትከያ አስገድዶ ማስለቀቅ ይቻል ነበር፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ባለመሬቱ ማዘጋጃ ቤቱን በመሬቱ ለውጥ ከጠየቀ የተወሰደበትን ቦታ ደረጃና መጠን የጠበቀ የቦታ ለውጥ ይሰጠዋል፡፡

ቦታው ሲወሰድ የግምት ክፍያ የሚሰጠው ለመሬት ሲሆን ማዘጋጃ ቤት ዋና ዋና ጠቃሚ የሆኑትን ቦታዎች በካዳስትር ክፍል አማካይነት ቀደም ብሎ የቦታውን ደረጃና የአንድ ሜትር ካሬ ዋጋ ተምኖ ባስቀመጠው መሠረት ነበር፡፡ ባለቤቱ ለመሬቴ የመሬት ለውጥ ነው የምፈልገው ካለ ደረጃው እኩል የሆነና ስፋቱም በተወሰደበት ልክ ተለክቶ ሌላ መሬት ይሰጠዋል፡፡ የራሱን ቦታ ከማስረከቡ በፊትም አዲሱን ቦታ ይረከባል፡፡

በቦታው ላይ ንብረት ካለና በፈቃድ የተሠራ ቤት ከሆነ ማዘጋጃ ቤቱ ለቤት ሥራ ፈቃድ ክፍል ካስመዘገበው የመሥሪያ ዋጋ ላይ የአገልግሎት ቅናሽ አድርጐ ቀሪውን ይከፍለዋል፡፡ ያለ ፈቃድ የተሠራ ቤት ከሆነ ገማች መሐንዲሶች ተልከው በገመቱት መሠረት ግምቱ ይከፈለዋል፡፡

## *በፕላን ክፍል ያጋጠመኝ ተጨማሪ የሥራ ጫና*

እኔ ማዘጋጃ ቤት ፕላን ክፍል ስገባ ከነበሩት ውዝፍ ሥራዎችና የየዞኑን ባለጉዳይ ከማስተናገድ በተጨማሪ አምስቱ (የየወረዳው) ማዘጋጃ ቤቶች እራሳቸውን ችለው እንዲተዳደሩ የተወሰነበት ጊዜ ስለነበር ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ለያንዳንዱ የክፍል ማዘጋጃ ቤት ሠርተን ማስረከብ ነበረብን፡፡

1) ለያንዳንዱ ማዘጋጃ ቤት ክልል ወሰኑን ለይቶ የሚያሳይ ፕላን ማስረከብ፣
2) ወደየማዘጋጃ ቤቱ የሚላኩትን መሐንዲሶች ማዘጋጀት፣
3) እራሳቸውን ችለው መወሰን የሚችሉበትን መምሪያ ማዘጋጀት፣
4) ወደየማዘጋጃ ቤቱ የሚሄዱትን መሐንዲሶች መርጦ ስልጠና መስጠት፣
5) እስከ 10,000 (አሥር ሺህ) ብር ለሚአወጡ ቤቶች የፕላን ማሠሪያ መክፈል ለማይችሉ ሰዎች በነፃ የሚሰጡ የተለያዩ የቤት ፕላኖች ማዘጋጀት (ይኸውም ለከተማው የቤት አሠራር አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ ነው።)
6) የተቻለውን ያህል በፕላን ላይ ያሉትንና ደግሞም የልማት እንቅስቃሴ አለበት በተባሉት ቦታዎች ላይ ነባርና አዲስ የፕሮጀክት መንገዶችን ነድፎ ለየክፍሉ መስጠት የክፍላችን ዛላፊነት ስለነበር ያለምንም እረፍት መሥራት ነበረብን። በትርፍ ሰዓትም ጭምር ማለቴ ነው። በዚህ አጋጣሚ ጀርመን አገር ተልኬ ስለሎካል ገቨርንመንት ያጠናሁትን ትምህርት በዚህ ሥራ ላይ ለማዋል እድል አጋጥሞኛል።

## *የኤሌክትሪክ አውቶቡሶችን በተመለከተ (የግል ጥናት)*

በ1961 ዓ.ም. ስለከተማ ውስጥ ትራንስፖርት በፕራግ (የቀድሞው ቼኮዝሎቫኪያ፣ ያሁኗ ቼክ ዋና ከተማ) ውስጥ ሁለት ወር የወሰደ አለም አቀፍ ሴሚናር ላይ ተሳትፌ ነበር። በዚሁ ወቅት ለአገራችን ጠቃሚ ናቸው በምላቸው ጉዳዮች ላይ ብዙ ኢንፎርሜሽን ሰበሰብኩ። ከነዚህ ውስጥም በጣም የማረከኝና ጠቃሚ ሁኖ ያገኘሁት በኤለክትሪክ የሚነዳው ባለጎማ አውቶብስ ነበር (ባለሐዲድም ነበር)።

በአገራችን እግረኛ ስለሚበዛ በናፍጣ የሚነዱት አወቶቡሶች በቂ አገልግሎት እንደማይሰጡ ስለማውቅ አማራጭ ሊሆን ይችላል ብዬ የገመትኩት የኤሌክትሪኩን አውቶብስ ወደ አገራችን ማምጣት ነበር። ጥቅማቸው እንደሚከተለው ነው።

1) አገራችን በውሃ ኤሌክትሪክ ስለምታመነጭና ትርፍ ኃይልም ስላለን በሱ ለመጠቀም፣
2) ለአወቶብሶች ናፍጣ ከመግዛትና ከተማዋን በጭስ ከመበከል ስለምንድን፣
3) አንዱ ፋርጎ ከ70 ሰው በላይ ስለሚጭን፣
4) እንደ ተጠቃሚው ብዛት ሁለት ፋርጎ በአንዴ ቀጣጥሎ ስለሚሄድ፣
5) ፕራግና አካባቢዋ ዳገታማ ስለሆኑ የኛም አገር የዚያው ዓይነት ስለሆነ፣ ወደኛ ቢመጣ ሊሠራ ስለሚችል፣
6) ለናፍጣ መግዣ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ስለሚያድን፣

7) የፉርጐው የውጭና የውስጥ ዕዳት ጥሩ ስለሆነና ለተሳፋሪው ምቹ በመሆኑ ሁሉም ሰው ሊጠቀምበት ስለሚችል፣

8) ይህንኑ አውቶብስ መስኮቦችና ሌሎችም የሰለጠኑ አገሮች የሚጠቀሙበት ስለሆነ፣

9) ቼኮችን ሳነጋግራቸው በራሳቸው ገንዘብ አስፈላጊውን ጥናት ሁሉ አገራችን መጥተው ሊያጠኑልን ፈቃደኛ ስለሆነኑና፣

10) ማሽኖቹ ፕራግ ውስጥ በሚዘጋጁበት ጊዜ ከኛ ሰዎች ወስደው እንደሚያስለጥኑልን ስላረጋገጡልኝ ከስፍራው የአውቶብሱንና የፉርጐውን ፎቶግራፍና ሌላም ማስረጃዎች ይዤ በመምጣት ሪፓርቴን አዘጋጅቼ እንደተለመደው በቀጥታ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቀረብኩ፡፡ ፎቶግራፉንም አሳየኋቸው፡፡ ጃንሆይም ይህንማ ብትሠራ ከተማዋን ፈረንጅ አገር አረግካት ማለት ነበር ካሉ በኋላ ታዲያ ምን ይሻላል በሚል ጠየቁኝ፡፡ እኔም ለሥራና መገናኛ ሚኒስቴር ቢሰጥና እዚህ ካለው ከቼኮዝሎቫኪያ አምባሳደር ጋር ተነጋግረው ቢጨርሱ ይሻላል አልኩ፡፡ እሳቸውም መልካም አሉ፡፡ በነጋታው ለሥራና መገናኛ ሚኒስቴር ሲጻፍ ለኔም ግልባጭ ደረሰኝ፡፡

ከወራት በኋላ ይመስለኛል ኤክስፐርቶቹ አዲስ አበባ መጡ፡፡ ከኔ መስሪያ ቤትም ትራንስፖርት ሊገባባቸው የሚገባቸውን ዋና ዋና መንገዶች በፕላን ነድፈን ሰጠናቸው፡፡ በዛ መሠረት በጐማ የሚሽከረከሩት ከየት እስከየት እንደሆነ በብረት ሀዲድ ላይ የሚሽከረከሩት ደግሞ በየትኛው መንገድ ላይ እንደሆነ ከነዝርዝር ጥናቱ ዋጋውንና ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚጠይቀውን ጊዜ ጭምር (ከቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴ ዩኒቨርስቲ ጋር ሆነው) አቀረቡልን፡፡ የቀረው ነገር ቢኖር ስምምነቱን ተፈራርሞ ሥራ መጀመር ብቻ ነበር፡፡ ለጠቅላላው ሥራ የተጠየቅነውም ዋጋ 7,920,000 ብር ነበር፡፡ ጥናቱን ለማድረግ ከራሳቸው 200,000 (ሁለት መቶ ሺ.ህ) ብር አውጥተዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከተማችን በኛ አቆጣጠር በ1975 ዓ.ም የኤሌክትሪክ አውቶብሶች ይኖሩን ነበር፣ የ1966ቱ የመንግሥት ለውጥ ባያደናቅፈው ኖሮ፡፡

## ሌላው ሰፊና ጠቃሚ የግል ጥናት

እኔ ወደ ፕላንና የቤት ሥራ ፈቃድ ክፍል ከተዛወርኩበት ቀን ጀምሮ ለአእምሮዬ ሰላም የሚሰጡ ሁኔታዎች አጋጥመውኝ ነበር ብዬ ለመናገር አልደፍርም፡፡ በእርግጥ ብዙ ትምህርትና የሥራ ልምድ የማገኝበት ባሕር ውስጥ እንደገባሁ አስቀድሞውንም ተረድቼ ነበር፡፡

ምናልባት ከፍተኛ ትምህርቴን ጀርመን አገር ስለተማርኩ ሊሆን ይችላል ሥራ ያሸንፈኛል ብዬ አስቤም አላውቅም፡፡ ሌላም ከዛ አገርና ሕዝብ የተማርኩት ሥራን ዝግ ብለህ ሥራ ነገር ግን በምትሠራው ሥራ እርግጠኛ ሁን የሚለውን ዘይቤያቸውን ነበር፡፡ እኔም በሥራዬ እርግጠኛ ለመሆን አይኔን፣ ጆሮዬን፣

አእምሮዬን ክፍት አድርጌ እጠቀም ነበር። ከመደበኛ ሥራዎቼ ውጭም ምን እየተሠራ ነው ብዬ በመታዘብ መመራመሬ አልቀረም።

ከነዚህ ከታዘብኳቸው አንዱ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎችና ሐብታሞች በገዛ አገራቸው በጥናትም ሆነ በኮንስትራክሽን መስክ የውጭ ተወላጆችን በጨረታ አሸንፈው ወደ ፕላንና የቤት ሥራ ፈቃድ ክፍል አለመምጣታቸው ነበር። አሸናፊ ሆነው ሥራውን ሁሉ የሚይዙት የውጭዎቹ ብቻ ናቸው።

በዚህን ጊዜ በምቀኝነት ሳይሆን በወገኖቼ መጠቃት እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው የአገራችን ሀብት በውጭ ተወላጆች እጅ ውስጥ መግባቱ በጉ ቅናት አሳደረብኝ። ለዚህም መፍትሄ ማፈላለግ ጀመርኩ። ያለው አማራጭ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉን የመሥራት መብት የተሠጠው ከነሱ ኩባንያዎች ጋር መወዳደር የሚችል ኩባንያ ቢቋቋም በተለያዩ ቦታዎች ሁሉ የወገኖቼንና የአገሪቱን ሀብት መቆጣጠር እንደሚችል አመንኩ።

ስለሚአስፈልገውም ካፒታል ሳጠና በፊት የጠላት ንብረት በኋላ ደግሞ የመንግሥት ንብረት ምንስቴር ተብሎ በሚኒስትር ዲኤታና በምክትል ሚኒስትር የሚመራ መስሪያ ቤት ብዙ አሮጌና ጥቂት አዳዲስ ቤቶች እንዳለውና በርካታ ለልማት ምቹ የሆኑ የከተማና የገጠር መሬቶችን እንደሚያስተዳድር አወቅሁ። ግን ቤቶቹ ገቢያቸው አመርቂ እንዳልሆነ ስረዳ እነዚህን ንብረቶች ለማግኘት አስቸጋሪም እንደማይሆን ተገነዘብኩ።

ሁሉም ነገር የተመቻቸ በመሆኑ እንደ ልማዴ ሁለገብ ኩባንያውን ለማቋቋም ማስታወሻ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቀረብኩ። እሳቸው የሰውን ሃሳብ ከመቅጽበት ለመረዳት አእምሮ የታደላቸው ንጉሥ ነበሩ ብል አልተሳሳትኩም። ችግሩም ሆነ መፍትሔው ስለገባቸው «የጠፋው ሰው እንጂ ሥራው አይደለም አሉና ታዲያ የሚሻለው ምንድነው» አሉኝ። እኔም ከመንግሥት ንብረት የተወሰነ ቤትና ቦታ በካፒታልነት የምአስመዝግበው ቢፈቀድ በንግድ ሕግ ኩባንያውን ማቋቋም ይቻላል በማለት ምላሽ ሰጠሁ። ግርማዊነታቸውም ይሁን ፈቅደናል ለገንዘብ ሚኒስቴር ይጻፍለት ጉዳዩንም አንተ እንድትከታተል አሉኝና ደስ ብሎኝ ልወጣ ስል በዚሁ ቀጥል እግዚአብሔር ይርዳህ ብለውኝ ወጣሁ። ጥናቴንም ሆነ ኩባንያው እንደሚቋቋም ለማንም አልተናገርኩ። ከጥቂት ቀን በኋላ አቶ ጌታቸው ማኀተመ ሥላሴ ወደ መንግሥት ንብረት ሚኒስቴር ተዛውረው ባሳሰቡት መሠረት ኩባንያውን እንዲያቋቁሙ የሚል ደብዳቤ ከጽህፈት ሚኒስቴር ለከንቲባው ሲደርሳቸው ወዲያውኑ ቤተመንግሥት ሄደው አቶ ጌታቸው አይዛወርብኝ ለሥራዬ እፈልገዋለሁ ብለው ሲጠይቁ (እንደተነገረኝ የተሰጣቸው መልስ) ድሮውኑ ደህና አድርገህ በያዝከው ነበር የሚል ነው።

## 3. ተጨማሪ የሥራ ልምድ

እኔም የማዘጋጃ ቤት ሥራዬን አስረክቤ ወደ መንግሥት ንብረት ሚኒስቴር ተዛውሬ አዲሱን ሀላፊነቴን በ1957 ዓ.ም ጀመርኩ።

በመስሪያ ቤቱ ብዙ ዋና ዴሬክተሮችና ዲሬክተሮች የክፍል ሃላፊ ሆነው ይሠሩ የነበረ ቢሆንም እኔ የነዚሁ ሁሉ ኃላፊነት እንዳለኝ ተገልጦ ሠርኩላር ደረሰኝ። የኔ ፍላጐት የመጣሁበትን ጉዳይ ለማከናወን ስለሆነ ሥራዬ ላይ አተኮርኩ። በካፒታልነት ለመመዝገብ የሚችሉትን ንብረቶች መምረጥና ማደስ ዋና ስራዬ አደረግሁ።

በአሠራሬ የሚአውቁኝ ሰዎች ለአለቆቼ ደህና ሰው መጣላችሁ ሲሏቸው መጣባችሁ በለን እንጂ ምን መጣላችሁ ትለናለህ ያሉም አልጠፉም። ከሥራ ጫና የተነሳ ከብሔራዊ ባንክ የፋይናንስና የሕግ ሰዎች የኩባንያውን ማቋቋሚያ ደንብ በእርዳታ ያዘጋጁልን ነበር።

ንብረቶቹን ለማየትና ለማሳደስ በጠቅላይ ግዛቶች ጭምር እየተዘዋወርኩ መደረግ ያለባቸውን ሁሉ አመቻቸሁ። የኩባንያው ቦርድ አባሎች ተመረጡ። የተመረጡትም ለኩባንያው የሥራ እንቅስቃሴ ሊአግዙ ይችላሉ ከተባሉት የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ነበር። ኩባንያውም ብሔራዊ ሀብት ልማት ኮርፓሬሽን ሼር ካምፓኒ (ብሀል) በሚል ስም ተጠራ።

ለኩባንያው የበላይ ጠባቂ የገንዘብ ሚኒስትሩ ስለነበሩ ለኩባንያው ሥራ ኃላፊ እንዲሆኑ የመንግሥት ንብረት ሚኒስትር ዲኤታውን ማናጂንግ ዲሬክተር፣ ምክትል ሚንስትሩን ደግሞ ጄኔራል ማናጀር አድርገው በመሾም እኔን ጨርሶ በመስሪያ ቤቱ እንዳለሁም ሳይቆጥሩኝ ቀሩ። አድራጐቱ ለኔ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ግራ ያጋባ ነበር።

በጽሕፈት ሚኒስቴር ወደ መንግሥት ንብረት ሚኒስቴር የተዛወርኩበት ደብዳቤም ተረሳ። ነገሩ ሆን ተብሎ የተደረገና የበላዮቼን ላለማሳዘን መሆኑ ስለገባኝ ከቢሮዬ ያሉኝን የግል እቃዎቼን ይዤ የምገኝበትን የስልክ ቁጥር ለጽ/ቤቱ ሰጥቼ ሥራውን ትቼ ቤቴ ተቀመጥሁ።

ለወራት ያህል ሁኔታውን እቤቴ ሁኜ ተመለከትኩ። ጉዳዩ ዝምታ የሰፈነበት ሁኖ ስላገኘሁት የራሴን የኑሮ እቅድ አወጣሁ። ይኸውም ከባንክ ተበድሬ ለአምስት አመት ግዴታዬን ስከፍል የቀየሁበትን ቤቴን ሽጬ እዳዬን ከከፈልኩ በኋላ በሚተርፈኝ ገንዘብ ገበሬ መሆንን መረጥኩ። ዱግዳ ወረዳ ውስጥ (ዝዋይ ሀይቅ አካባቢ) በመቂ ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ የግብረጠል መሬት በጨረታ ሲሸጥ አምስት ጋሻ መሬት በሶስት ሺህ ብር አሸንፌ ገዛሁ። መሬቱ ደረቅና አሸዋማ የሆነ ግብርና ላይ ያልዋለ አካባቢውም ምንም ውሃ የሌለበት ልማትም ሆነ መንገድ የሌለው ነበር።

አሚራን ከሚባል የእሥራኤል ኩባንያ በከፊል ገንዘብ ከፍዬ ሌላውን በብድር የእርሻ መሣሪያዎች ገዝቼ እርሻ ጀመርኩ። እንቅስቃሴውን አሳይቼ ከልማት ባንክ ትንሽ ብድር አገኘሁ። ይኸውም የዘመዴን የአቶ አጥላው ወልደዮሐንስን ካርታ በማስያዝ ነበር።

የመጀመሪያው ሰብል አስደሳች ባይሆንም አላከሰረኝም። የሁለተኛውን አመት የአስተራረስ ዘዴ ሰብሶይለር በሚባል ልዩ ማረሻ በመጠቀም የዝናቡ ውሃ በጐርፍ መልክ እንዳይሄድ በጥልቀት እመሬቱ ውስጥ እንዲጠራቀም

በማድረጌና ሰብሉ ድርቅን እንዲቋቋም ስላደረግሁ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ምርት (በአንድ ሄክታር ስልሳ ኩንታል በቆሎና ሰላሳ አምስት ኩንታል ሚቺጋን የሚባውን ቦሎቄ) ማምረት ቻልኩ። ሰብሉን በጥሩ ዋጋ በመሸጥ ባገኘሁት ገንዘብ፦

1ኛ/ ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ አስቆፈርኩ

2ኛ/ ትንሽ ማረፊያ ቤት ሠራሁ

3ኛ/ መጋዘንና ጋራዥ ሠራሁ

4ኛ/ የሠራተኞች መኖሪያ ሠራሁ

5ኛ/ ከተረፈ ምርት በሚገኘው ተቀልበው የሚሰቡ ሰንጋዎች መግዛትም ቻልኩ።

የውሃ ጉድጓዱን ለማስቆፈር ገንዘብ ስላጠረኝ የኢንቨስትመንት ባንክም ትንሽ ገንዘብ አበድሮኛል። በዛን ዘመን በጥሩ ጥናት ለሚከናወኑ ሥራዎች ገንዘብን ከባንክ፣ እቃዎችን ከኩባንያዎች እንዲሁም የሰብል መሰብሰቢያ ገንዘብ ከኤክስፖርት አድራጊ ነጋዴዎች በቀላሉ መበደር ይቻል ነበር።

ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ጠንክሮ ከሠራ ሐብታም እንደሚሆን ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል። ኑሮ በመንግሥት መ/ቤት ደሞዝ ብቻ እንዳልሆነም ፈር ከቀደዱት ወጣት ባለሙያዎች አንዱ ስለነበርኩ በምሳሌነትም ልጠቀስ ችያለሁ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የብሔራዊ ሀብት ልማት ኮርፓሬሽን ሼር ካምፓኒ ተብሎ የተቋቋመው ኩባንያ ከአንድ አመት በላይ ሥራውን ከቀጠለ በኋላ በማንጁድ የኦዲተር ኩባንያ ኦዲት ሲደረግ በርካታ የአሠራር ስህተቶች ፈጽሞ በመገኘቱ ኦዲት ሪፖርቱ ለቦርዱ ሲቀርብ መደናገጥን እንደፈጠረ ይነገረኛል።

የቦርዱ ሊቀመንበር የገንዘብ ሚኒስትሩ ስለሆኑና የቀድሞውን የገንዘብ ሚኒስትር የተኩ ስለነበር የድርጅቱን ታሪክ ስለማያውቁት ኩባንያው እንዴት እንደተቋቋመ ጠይቀው በዝርዝር ተነገራቸው። በዚህን ጊዜ ቦርዱ የነበረው አማራጭ ታሪኩን ከመሠረቱ የማውቀውና ጥናቱንም በዋናነት ያቀናበርኩት እኔ ስለነበርኩ አሁንም ጌታቸው ማኀተመ ሥላሴ ተፈልጐ እንዲአስተካክለው በማለት መወሰን ነበር።

በሥራው ላይ ከፍተኛ ኃላፊ ከነበሩት መሀል ሁለት የሕንድ ተወላጆችንና የርስት ክፍሉን ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ ባለሥልጣን በረዳትነት ይዤ ንብረቱንም ሆነ ገንዘቡን መልክ አስያዝኩ። የውጭ ተወላጆቹ ዋና አማካሪና የሂሳብ ክፍል ሀላፊ ነበሩ።

ለስህተቱ ዋናው ምክንያት የሆነው ሚኒስትር ዲኤታው ወይም ማናጂንግ ዲሬክተሩ የመንግሥት ንብረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን በተጨማሪ ያዙ ስለነበር ሂሣቡንም ሆነ ንብረቱን የካምፓኒውን ከሚኒስቴሩ ጋር በመደበላለቅ

ማዘዛቸው ነበር፡፡ ሌሎቹ ባለሥልጣኖች ደግሞ ኩባንያው መቋቋሙን እንጂ የተቋቋመበትን አላማ ከሥር መሠረቱ ስለማያውቁት ሥራውን በተገቢው መንገድ አላስኬዱትም፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ኩባንያው ግቡን ሊመታ አልቻለም፡፡

እኔም ጥናቴን ካደረግሁ በኋላ ሪፖርቴን ለቦርዱ አቀረብኩ፡፡ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥም በቦርዱ ተጠርቼ ስራዬን ካመሰገኑ በኋላ ቀጠል አድርገው አንተን የኩባንያው ሥራ አስኪያጅ እንድትሆን እንፈልጋለን ምን ይመስልሃል አሉኝ፡፡ እኔም እነዚህ ሁለት ታላላቅ ባለሥልጣኖች ተነስተው እኔ ለሥራው በሐላፊነት እመረጣለሁ የሚል ሃሳብ ስላልነበረኝ ትንሽ ደነገጥኩ፡፡ የሰጠሁትም መልስ ስለጠፋኝ ጌቶቼ እንዳስብበት አንድ ሁለት ቀን ስጡኝ ብዬ መጠየቅ ነበር፡፡ እነሱም ፈቀዱልኝ፡፡

ወዲያው ያልወሰንኩት የአባቴን ምክር ለመጠየቅ ነበር፡፡ ለአባቴም ሁኔታውን ካስረዳሁ በኋላ እሱም እነዚህ ሁለቱ ባለሥልጣኖች አንተ እንዲቋቋም ካደረግከው ኩባንያ ያስወጡህ ስለሆነ እነሱ ተነስተው ያንተ መተካት የእግዚአብሔር ዳኝነት ነውና ተቀበል አሉኝ፡፡ ከሁለት ቀን በኋላም የቦርዱን ውሳኔ አመስግኜ ውሳኔአቸውን ተቀብዬ ሥራውን በኃላፊነት ተረከብኩ፡፡

የኩባንያው አላማ ሥራዎችን በሁሉም መስክ ተጫርቶ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ስለነበር ቅድሚያ የሠጠኋቸው ሥራዎች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ነበሩ፡-

1) ኩባንያው ሲቋቋም ያገኛቸውን ንብረቶች በጥሩ ሁኔታ በማደስ ጥሩ ገቢ እንዲሰጡ ማድረግ፣
2) የእርሻ መሬቶችን በግልና በማኅበር ሥራ ላይ ለማዋል እቅድ ማውጣት፣
3) የኮንስትራክሽን ሥራዎችን ማጠናከር፣
4) ያሉትን ቤቶችና መሬቶች ማከራየት፣
5) ከሌሎች ባለሀብቶች ጋር ኩባንያ መስርቶ በስፋት መስራት...ነበር፡፡

በዛን ዘመን የነበረው የኢንቬስተሮች ትኩረት ዛሬ ኢንቨስት አድርገው ነገ ትርፍ በሚሠጡ ንግዶችና ሥራዎች ላይ ብቻ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ረዘም ላለ ጊዜ ደክመው ለረጅም ጊዜ ባለማቋረጥ በርካታ ቋሚ ገቢ ወደሚሠጡ ልማቶች ፊታቸውን እንዲመልሱና አገሪቱም እንድትለማ ግፊት አደረግን፡፡

ጥሩ የስራ ውጤት ለማግኘት ደግሞ ጥሩ ጥሩ ባለሙያዎች እንዲኖሩን ያስፈልጋል፡፡ እሱም ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ በቅድሚያ በኃላፊነት ላይ የሚመደቡትን የመሥሪያ ቤት ባለሙያዎችን ቀጠርን፡፡ ለምሳሌ የፋይናንሱን ሰው ስንቀጥር ከውጭ ታዋቂ ኦዲተሮችንና መልካም ስም ያተረፉ የፋይናንስ ባለሙያዎችን እንዲፈትኑልን በመጋበዝ ሲሆን የኢንቨስትመንት ኃላፊዎችን፣ የእርሻ ክፍል ኃላፊዎችን፣ የአስተዳደርና የኮንስትራክሽን እንዲሁም የቢዝነስ ባለሙያዎችን ፈትነው የመረጡልን በተመሳሳይ ሙያቸው ታዋቂ ከሆኑ

መስሪያ ቤቶች የተውጣጡና ኮንስልታንቶች ነበሩ:: ለባለሙያዎቹ የደመወዝ ክፍያም ከኃላፊነታቸው ተመጣጣኝ ነበር::

ከኃላፊ እስከ ተራ ሠራተኛ ድረስ ሥራውንና ኃላፊነቱን የሚገልጽ መመሪያ በሥራችን ራዕይ መሠረት በውጭ አጥኚ ኩባንያዎች አዘጋጅተን ለሁሉም አደልን:: ሥራም ላይ ዋለ::

ሥራውን የተረከብኩት በአመት አጋማሽ ላይ ስለነበር በዓመቱ መጨረሻ ኦዲት ሲደረግ ጥሩ የሥራ እንቅስቃሴና አጥጋቢ የሆነ ትርፍ መገኘቱን ቦርዱ ከኦዲት ሪፖርቱ ላይ በመረዳቱ ድጋፉን ለግሶኛል::

ኩባንያው ሲያካሂዳቸው ከነበሩ ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ:-

1) የአባድር የጥጥ እርሻ ከእስራኤሎች ጋር፣
2) የመልካ ሰዲ የሙዝ እርሻ ከኢጣልያኖች ጋር፣
3) የሥጋ ንጥር ከጃፓኖች ጋር፣
4) በበቃ የተቋቋመው የቡና ተክል ሥራ ከፈረንሳዮችና ጣልያኖች ጋር፣
5) የጉለሌ የብርጭቆና ጠርሙስ ፋብሪካ ከኢንቬስትመንት ባንክና ከግለሰቦች ጋር፣
6) ሠንቀሌ ላይ በ3,000,000 ብር አዲስ የተቋቋመው የአምቦ ውሀ ፋብሪካ አዲስ በኩባንያችን ብቻ የተሠራው፣
7) የውሽውሽ የሻይ ተክል ጥናት በኩባንያችን የውጭ ኤክስፐርቶች ተጠንቶ ከአፍሪካ ዲቨሎፕመንት ባንክና ከእርሻ ባንክ ብድር ለመስጠት የተስማሙበት ጥናት፣
8) ሆቴሎችና መዝናኛ ስፍራዎችን (ኢትዮጵያ ሆቴል፣ አዲስ አበባ ፍልውሃ ሆቴሎችና መዝናኛዎች፣ ሶደሬ፣አምቦና አዋሳ ፍልውሃና መዝናኛዎች ይርጋለም ጊዳቦ በሚባለው ፍልውሃ ላይ ያለውን መታጠቢያና ሌሎችንም) ማሻሻል፣
9) ሕንፃና ሌሎችንም የኮንስትራክሽን ሥራዎች ያጠቃለለ Real Estate Development ሼር ኩባንያ ከእርሻ ባንክ ጋር፣
10) ከሳባ የጠጅ ፋብሪካ ጋር የተቋቋመው የአባድር የወይን ጠጅ ምርት፣
11) ካዋሳ የእርሻ ጣቢያ ጋር የቃጫ ተክል ልማት፣
12) ሊሙ ውስጥ ያሉን የቡና ልማት እርሻዎች፣
13) አባድር ላይ ሰፊ የፍራፍሬ እርሻ፣
14) የውድቅዳቂ ብረቶች ማቅለጫ ፋብሪካ (ከጣሊያኖች ጋር)
15) ጊዳቦ ላይ የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ ለማቋቋም ጥናቱ ያለቀና ማሽኒያው የተዘጋጀ፣

16) ትሬዥሪ ቢል ከመንግሥት ተጫርተን መግዛት፣

17) ከቡልጋርያኖች ጋር መተማ ላይ የከብት እርባታንና እርሻ ለማቋቋም ተስማምተን እነሱ ቦታውን ከጐበኙ በኋላ መንገዱንም እራሳቸው ሊሠሩልን ድርድሩ መጠናቀቅ ላይ የነበረ።

እነዚህ ሁሉ በጥሩ ሁኔታ አትራፊ ኩባንያዎች ነበሩ። ለምሳሌ አባድር የጥጥ እርሻ እኛ ሁለት መቶ ሺህ ብር እስራኤሎች ሁለት መቶ ሺህ ብር ካፒታል ያዋጣንበት ኩባንያ ነበር። አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ብር ንፁህ ትርፍ አግኝተን ትርፉንም ለሠራተኞች መኖሪያና ለርሻው ማስፋፊያ አውለናል።

ከጃፖኖች ጋር በሁለት መቶ ሺህ ብር ያቋቋምነው የሥጋ ንጥር ኩባንያ በአመቱ መጨረሻ ካፒታሉን መልሶ 200,000 ሺህ ብር ንጹህ ትርፍ በማስገኘቱ በትርፉ ካፒታሉን አሳደግን።

እነዚህ የውጭ አገር ኢንቨስትሮች ከብሔራዊ ሀብት ልማት ኮርፖሬሽን አክሲዮን ማህበር ጋር ለመሥራት እጅግ ፈቃደኛ የሆኑት ያለምክንያት አልነበረም። ይኸውም

1) የልማት መሬት ለመምረጥና የፈለጉትንም ያህል በስፋት ለማግኘት እድል ስለነበራቸው፣

2) ዋጋውም እንደ ግል ሻጭ ባለርስቶች ውድ ባለመሆኑ እኛም በዝቅተኛ ዋጋ የሚሸጠው መሬት ለራሳችን ኩባንያ በመሆኑ ሁለታችንም ተጠቃሚ በመሆናችን፣

3) ከባንክ ለመበደር ኩባንያው ታማኝነት ስለነበረው በቀላሉ ለማግኘት ስለሚቻል፣

4) በሥራ ላይ ለሚአጋጥሙን ችግሮች በቦርዱ አባሎች አማካይነት ቶሎ መፍትሄ ለማግኘት ስለሚቻል፣

5) በታክስና ወደ ውጭ በትርፍ ሰበብ የሚወጡትን ገንዘቦች መንግሥት በኛ አሠራር ምክንያት የመቆጣጠር እድል ስላጋጠመው የመንግሥት ድጋፍ አልተለየንም ነበር።

6) ለአገሪቱ እጅግ ጠቃሚና ተፈላጊ የሆኑ ከባድ ካፒታልና የረጅም የውጤት ጊዜ ለሚጠይቁ ልማቶች የግል ኢንቨስተሮች መሳተፍ ስለማይፈልጉ በተቻለ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ እኛ በመያዝ በማግባባት አብረውን እንዲሠሩ ለማድረግ ችለናል።

7) መንግሥት ወይም የአለም ባንክ በረጅም ጊዜና በአነስተኛ ወለድ የሚከፈል ብድር ለኛ ባንኮች ሲሰጥ እኛ ደግሞ ከኢንቬስትመንት ባንክና ከልማት ባንክ በመበደርና አብሮ ኩባንያ በማቋቋም ገንዘቡን ልማት ላይ በማዋል አገሪቱን ለመጥቀም ችለን ነበር።

8) በእርሻና በኢንዱስትሪ ልማት ከውጭ ካፒታሊስቶች ጋር ኩባንያዎች ስናቋቁም ልምድ እስከምናገኝ በመጀመሪያ ጊዜ በኃላፊነት ላይ የኛ ልጆች አብረው ዝግጅቱ ላይ እንዲሳተፉ ቀጥሎም ተግባር ላይ

በሚያውሉበት ወቅት አብረው እየሠሩ እንዲለማመዱ በማድረጋችን እንዲሁም ወደ ውጭ አገር ልከን በማሰልጠናችን ወጣት ማናጀሮቻችን ባጭር ጊዜ ውስጥ ኃላፊነቱን መረከብ ችለዋል።

9) ይህ ብሔራዊ ኃብት ልማት ኮርፖሬሽን ሼር ካምፓኒ ተብሎ በመሥራት ላይ የነበረው ኩባንያ ምን ያህል ጥራት ያለው አስተዳደርና ባለሙያዎች እንደነበሩት የሚያስረዳውና የሚያረጋግጠው ደርግ ስልጣኑን ሲይዝ በኢትዮጵያ ውስጥ የተወረሱ የእርሻ ልማቶችን፣ ቤቶችንና ሆቴሎችን እንዲሁም ሌሎችንም የግል ድርጅቶች ተረክቦ እንዲአስተዳድር ብቁ ሆኖ የተመረጠ መሆኑ ነው።

በኩባንያው የሥራ ኃላፊ የነበሩትም በሚኒስትርነትና በኮርፖሬሽን ኃላፊነት ደረጃ ተመርጠው ለመሾም በቅተዋል።

## *ሌላው የግል ጥናቴ - ቁጠባ ቤቶች*

የገበሬዎችን የቁጠባ ቤቶች አሠራር በጥሩ ሁኔታ ሊለውጠው ይችላል ብዬ ባሰብኩት ላይ ነበር ጥናት ያደረግሁት። በአገራችን በተለይም ከመተሐራ ጀምሮ እስከ ደብረዘይት እንዲሁም ወደ ዝዋይ በሚወስደው መንገድ አካባቢ በብዛት በሚገኘው ፖሚሽ (ቀላል የቮልካኒክ አመድ) ላይ ነበር ጥናቴን ከቡልጋሪያኖች ጋር የጀመርኩት።

የዚህንም የአፈር ናሙና ከተለያዩ ቦታዎች ወደ 5 ኩንታል የሚሆን ሶፍያ (የቡልጋርያ ዋና ከተማ) ወደሚገኘው Strojexport ወደተባለው መንግሥታዊ ድርጅት ልከን ውጤቱ አጥጋቢ እንደሚሆን አረጋገጡልን።

የመጀመሪያው እቅድ ከሣር ከገለባና ከጥቂት ሲሚንቶ ጋር ይህንን ፓሚስ በመደባለቅ በሳንቃ ደረጃ ፓኔል ማምረት ነበር። የዚህ ሣንቃ መሰል ፖኔል ጥቅም የጭቃ ቤታቸውን የሚተካ እንዲሁም በከተማ ውስጥ ለተለያዩ የቁጠባ ቤቶች መሥሪያና የውስጥ ክፍሎችን ለመከፋፈያ የሚውል ነበር። ክብደት የሌለው፣ ድምጽ የማያስተላልፍ፣ ውሃ የማይመጥና እሳትን የሚቋቋም መሆኑ ሌላው ጥቅሙ ነበር። ከማምረቻ ቦታ እስከ 100 ኪሎ ሜትር ትራንስፖርት አድርጐ አገልግሎት ላይ ቢውል አትራፊ መሆኑ ታውቋል።

የቀረው ጥናት የማምረቻውን መሣሪያ ከየት እንግዛ የሚለው ነበር።ፕሪካስት ኮንክሪት ከሚአመርቱ ከእንግሊዝ፣ ከጀርመንና ከጣሊያን አምራች ድርጅቶች ጠይቁ ካታሎግ ካስመጣሁ በኋላ ጀርመን ያለውን ማምረቻ ለማየት እድል አጋጥሞኛል። ግማሹ በፋብሪካ መልክ አንድ ቦታ ተቋቁሞ በሚሰጣቸው ዲዛይን ሠርቶ የሚአስረክብ አይነት ሲሆን ሌላው ደግሞ ኮንስትራክሽኑ ቦታ ላይ የሚሠራ ነበር። የቁጠባ ቤቶችንም አስፈላጊነትና የዚህን ጥናት ፋይዳ የሚገልፅ አጭር ሪፖርት ለግርማዊነታቸው አቀረብኩ። ከዚሁ ሪፖርቴ ጋር አንድ ዜኒት የምትባል መሽን በሶስት ባለሙያዎችና ብቻ የምትካሄድ ብሎኬት፣ የጭስ ማውጫ ቱቦዎችን፣ የመንገድ ዳር ኮርዶኖችን፣ የወለል ንጣፍ ኮንክሪትን ትሠራለች። ዋጋዋ ደግሞ በአጠቃላይ ዘጠና ሺህ ብር መሆኑን፣ ስለ ሲም አሠራር የሚአሣይ ከ8 ሚሊ ሜትር ፊልም ጭምር ከአምራቹ John

Rieckerman ከተባለው ኩባንያ ያመጣሁትን ፊልም እንዲአዩ ለጃንሆይ ሰጥቼአለሁ፡፡

ስለዚህ መሣሪያ ከኔ የተረዱ ወዳጆችን ሲኖር ሪሶ ወዲያውኑ ከጀርመን አገር ገዝተው በማምጣት ኮሎናልፒ ላይ ተክለውት ይገኛሉ፡፡ አላማችን ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ ለግርማዊነታቸው በሪፓርቴ ውስጥ እንዳቀረብኩት፡-

1) የመንግሥት ሠራተኞች እና
2) በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት ባለቤት ይሆኑ ነበር፡፡ ሪፖርቴም ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች ከደምወዛቸው በየጊዜው እየተቆረጠ ቢከፈል ይሻላል የሚል ሀሳብ ቀርቦ ነበር፡፡ አንፈልግም ቢሉ እንኳ እራሳቸውን ለማስቻል የተደረገ በጐ ሐሳብ ስለሆነ ተገደውም ቢሆን ሃሳቡን እንዲቀበሉ በማድረግ የቤት ባለቤት ማድረግ ያስፈልጋል የሚል አረፍተ ነገር ነበረበት፡፡ ይህ ሁሉ አብዮቱ ስለቀደመው በሐሳብ ደረጃ ቀረ፡፡ ሙሉው ሪፖርት ካቀረብኩት ፊልም ጋር ቤተመንግሥት ይገኛል፡፡

በዚያን ጊዜ እኔ የነበረኝ ምኞት ሥራዎችን ሠርቼ ውጤቱን ማየት ነበር፡፡ ከዚያ በላይም የሚአስደስተኝ ነገር ስላልነበር ሌላውን ችግር ሁሉ በመሸከም ጥናቶቼን በቀጥታ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በማቅረብ የመሥራት ፍላጐቴን ተወጥቻለሁ፡፡ በዚህም ግርማዊነታቸውንና ኃያሉ እግዚአብሔርን እስካሁን ድረስ እያመሰገንኩ ነው፡፡

ጊዜውና ሁኔታው ፈቅዶ ቢሆን ኖሮ አሁን ኮንዶሚኒዮም የተባለው በጀርመኖች አጠራረ ሲድሉንግ የተባለውንና ከጭቃ ቤት ከፍ ያለ ጋርደን ያለው አንድ እንግዳ ከሌላ ቦታ ሲመጣ ኑሮውን እስከሚአመቻች የሚአርፍበት ተጨማሪ ክፍል ያለው፣ ልማት ሲመጣ ደግሞ የሚፈርስ ክላይን ጋርተን የሚባለውን ጭምር በጥናቱ መሠረት ተግባራዊ አደርግ ነበር፡፡ አሁንም ኮንዶሚኒየም ተግባር ላይ መዋሉ ያስደስተኛል፡፡

## 4. የ1966 ዓመተ ምህረት ሥር ነቀል የመንግሥት ለውጥና መዘዙ

የ1966 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ለአገሪቱና ለህዝቧ ጠቃሚ ነበር ወይም አልነበረም ስለሚለው የኢትዮጵያ ህዝብ ከእኔ የበለጠ ስለሚአውቀው አስተያየት ከመስጠት ተቆጥብያለሁ፡፡ ነገር ግን ሳልፈው የማልችለው ነገር ቢኖር ከ1955 እስከ 1966 ዓ.ም የነበረው የኢትዮጵያ ሁለገብ የልማትና የሥልጣኔ ፍጥነት መደናቀፍ በሁሉም አቅጣጫ እጅግ የጐዳን መሆኑን ነው፡፡

በተለይም አገርን አገር የሚአሰኛት የተማረ ሰው ሲሆን በአብዮቱ ወቅት ጥቃት የበዛው በምሁሩ ላይ ስለነበር የሞተው ህዝብ ሳይሆን የሞተችው አገራችን ኢትዮጵያ ነች ብል ስህተት አይደለም፡፡

እኔም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ባለስልጣን ነህ ተብለው ለእስር ከተዳረጉት አንዱ ነበርኩ፡፡ አብዮቱ ሲፈነዳ እንግሊዝ አገር ሄጄ ስለነበር በደርግ እንደምፈለግ ስሰማ ዳኝነት ያለ መስሎኝ ያለሁበትን አገር ጠቅሼ ወደ ኢትዮጵያ እንደምመለስ ቴሌግራም በማድረግ ከጥቂት ቀናት በኋላ ተመለስኩ፡፡

*ከአውሮፕላን ማረፊያ ወደአራተኛ ክፍለ ጦር ወስደው ከዛም ባለስልጣኖች ወደታሠሩበት ወደ ኮልፌ ተወስጄ ከታሰርኩበት ከሐምሌ 5/1966 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 1 ቀን 1974 ዓ.ም ድረስ ጥፋቴም ሳይነገረኝ እፍርድ ቤትም ሳልቀርብ ከ8 ዓመት በላይ እስር ላይ ቆየሁ። መስከረም 1/1974 ዓ.ም ሁላችሁም ከእስር ተለቃችኋል እቃችሁን ይዛችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ ተባልን።*

*ከጥቂት ቀን በኋላም አቶ ጌታቸው ማህተመሥላሴ አብዮቱን ያደናቅፋሉ ተብለው ስለተጠረጠሩ ከሐምሌ 1/1966 ዓ.ም ጀምሮ በቁጥጥር ስር ቆይተው በምህረት ተለቀዋል የሚል የምስክር ወረቀት ተሰጠኝ። ባጭሩ ኃጢአቴም ዳኝነቱም ይህን ይመስል ነበር።*

*ምንም እንኳ ፍርድ ቤት ሳልቀርብ ስምንት ዓመት ብታሰርም ኢትጵያዊነቴ ባለመገፈፉ ከተፈታሁ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ በውጭ አገር ድርጅቶች ተቀጥሬ ሠርቻለሁ። ያልበደለችኝን ኢትዮጵያንና ከግፍ አሠራሩ ውጭ የሆኑትን ወገኖቼን ከመርዳት የተቆጠብኩበት ጊዜ አልነበረም። መጀመሪያ የተቀጠርኩት በተባበሩት የአለም ቀይ መስቀል ማኅበርና በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን በተቋቋመው ከስደት ተመላሽ ኢትዮጵያውያኖችን መልሶ የሚያቋቁም ድርጅት ውስጥ ነበር። የፕሮጀክቱ አማካሪና የቴክኒክ ሥራ ኀላፊ ሁኜ በሠራሁበት ጊዜ በአገራችን በኤርትራ ውስጥ ተሰነይ ወረዳ ውስጥ አሊጊደር የተባለው የመስኖ እርሻ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ።*

*ቀጥሎም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን ጋር ባደረገው ስምምነት የስደተኞቹ የጤና አጠባበቅ ሥራና ከስደትም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ተቀብሎ የማስተናገዱን ጠቅላላ ኃላፊነት ሲፈራረም እኔን ሥራዎቹን ተግባራዊ እንዳደርግ ኃላፊ አድርጎ ስለሾመኝ በዚህም ጊዜ ውስጥ በተጓዳኝ ለአገሬና ለወገኖቼ ብዙ ጠቃሚ ሥራዎችን ሠርቻለሁ።*

*ስደተኛ ሲሠፍር ሐኪም ቤቱ፣ መመገቢያው አዳራሽ፣ የሐኪሞችና የባለሞያ ሠራተኞች መኖሪያ፣ መጋዘኖች ጋራዦችና ሌሎችም በመጠለያነት የሚያገለግሉት ድንኳኖች መሠራት ነበረባቸው። እኔ ሥራውን ከተረከብኩበት ጊዜ ጀምሮ እነዚህን በነፋስ በአይጥ፣ በሌባና፣ በዝናብ እየተበጣጠሱ በየአመቱ የሚለወጡትን የድንኳኖች መግዣ ሂሣብ በማውጣት ለአገራችን ቋሚ በሆኑ ዘመናዊ ህንፃዎች የሚተኩበትን ዘዴ በመንደፍ ከድንኳኖቹ መግዣ በሚመጣጠን ዋጋ ቤቶቹን ልሠራ እንደምችል ጥናት አቅርቤ በጀት አስፈቀድኩ።*

*ይኸውም ድንጋይና አሸዋን የመሳሰሉትን ከአካባቢው በነፃ በማግኘት የባለሞያ ጉልበት ደግሞ በመጠነኛ ክፍያ ከስደተኞቹ ውስጥ በመቀጠር ተነቃናቂ የብሎኬትና የአናጢ መሣሪያዎች በርካሽ ዋጋ ከአዲስ አበባ በመግዛትና በየፕሮጀክቱ ላይ የተመደቡትን መኪናዎች ናሙናዎች በመጠቀም 1ኛ. በጋምቤላ 2ኛ. በኢታንግ 3ኛ. በፉኝዶ 4ኛ. በከፋ ውስጥ በዲማ 5ኛ. በአሶሳ 6ኛ. በሐረር በባቢሌና በሌሎችም የስደተኛ ጣቢዎች ሁሉንም ዓይነት መገልገያዎች በአዲስ አበባ ቪላዎች አሠራር ደረጃ ለመስራት ቻልን።*

## *ሌላው የነበረኝ የሥራ ዕቅድ*

*በጋምቤላና በሌሎችም ክፍለ ሀገሮች ተዘዋውሬ በምሠራበት ጊዜ ለሕዝቡና ለአገሪቱ ጠቃሚ ነው በማለት ጥናት ያካሄድኩት ከሱዳን በሚያዋስኑን ክፍለ ሀገሮቻችን ውስጥ የሱዳን ሣር ተብሎ የሚጠራውን ሣር እጥቅም ላይ ለማዋል ነበር፡፡*

*ይህ ሣር በተጠቀሱት የአገራችን ክፍሎች በስፋት የሚበቅል ሲሆን ጠንካራ አገዳ ያለው ቁመቱ ከሁለት ሜትር በላይ የሆነ፣ አገሬው ለቤት ክዳንና አንዳንዴም ለግድግዳ ጭምር የሚጠቀምበት ነው፡፡ ጥቅም ላይ የሚውለው ሣር በአመቱ ከሚበቅለው አሥር እጅ (10%) አይሆንም፡፡ ቀሪውን ዘጠና እጅ (90%) ጥቅም ላይ ማዋል ሲቻል በእሣት እየለኮሱ ያቃጥሉታል፡፡ ይህም፣ ግልጥ በሆነ ቦታ ላይ የዱር እንስሳቶችን ለማደን እንዲያመቻቸው ነው፡፡ ቃጠሎው በአገሪቱ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ምሁራን ጭምር ሊገነዘቡት አለመቻላቸው በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡*

<u>ለምሳሌ</u>፡-

1) *ታዳጊ ዛፎችንና ወፍ ዘራሽ ችግኞችን ያቃጥላል፣*
2) *ከየዛፉ ላይ በመርገፍ ያረጁና የደረቁ ዛፎችን የሚተካው ዘር ተቃጥሎ ይወድማል፡፡*
3) *ቅጠላቸውን በመለብለብ ትልልቅ ዛፎችን ያደርቃቸዋል*
4) *ደርቀውና አርጅተው የወደቁትን ዛፎችም በማቀጣጠል የሰደድ እሳት እንዲነሳ ስለሚያደርግ የተፈጥሮውን ደን ከማውደሙ በተጨማሪ አካባቢውን የበለጠ በረሃማ ያደርገዋል፡፡*

*ቃጠሎውን በመሸሽ የዱር አራዊቶቻችን ወደ ጐረቤት አገር ወደ ሱዳን ይሰደዳሉ፡፡ ችግሩ በዚህ አላበቃም፡፡ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው የሚመጡት ከመቶ ሺህ በላይ አባወራዎች በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን መ/ቤት ለስደተኞቹ በየቦታው መጠለያዎች በሚአቋቁሙበት ጊዜ እያንዳንዱ የስደተኛ ቤተሰብ ጐጆውን፣ አጥሩንና የቤት እቃውን የሚሠራው እንደሁም ለማገዶ የሚአስፈልገውን እንጨት የሚአገኘው የተፈጥሮውን ደን በመመንጠር ቢሆንም፣ የተመነጠረውን የተፈጥሮ ደን የሚተካ አንድ ሰው እንኳን አልነበረም፡፡*

*እኔ በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽንና በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኀበር በተቋቋመው መ/ቤት ኃላፊ ሁኜ በመቀጠር ከተመደብኩበት ጊዜ ጀምሮ በየቦታው ስመላለስ ይህን አሳዛኝ ሁኔታ በመገንዘቤ መፍትሄ ለማግኘት ጥረት ከማድረግ አልተቆጠብኩም፡፡ የስደተኞችን ጣቢያ የሚያስተዳድሩት መሥሪያ ቤቶች የዛፍ ችግኝ እንዲአፈሉና ለስደተኛው ቤተሰብ በየደጃፉ የሚተክለው ችግኝ እንዲሰጡት ቢደረግም ውጤቱ ከሚደርሰው የደን ውድመት ጋር ጨርሶ ሊመጣጠን አልቻለም፡፡*

*የተሻለ ሆኖ ያገኘሁት ከሱዳን በሚአዋስኑ አውራጃዎቻችን ውስጥ የሱዳን ሣር ተብሎ የሚጠራውን ቁመቱ ከሁለት ሜትር በላይ የሚአድገውን ወፍራም ሣር በከሰል ምትክ ወደ ፊዩል ብርኬት* (FUEL BRIQUETTE) *በመለወጥ ለስደተኞቹ*

ማቅረብ፣ አለበለዚያም ለሚቆርጡት ዛፎች ስደተኞቹ በሚተክሉትና በሚንከባከቡት ደን ለመተካት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን በጀት እንዲያዝለት የማድረግ እቅድ ነበር። የዚህም እቅድ ውሳኔ በመዘግየቱ በተመሣሣይ ለአቅራቢያ ከተሞችና እንዲሁም አዲስ አበባን ለመሳሰሉ የማገዶ ችግር ላለባቸው ከተሞች ፊዩል ብርኬት የሚአመርቱ የግል ኩባንያዎች ቢቋቋሙ አትራፊ መሆኑን የሚገልጥ ጠቋሚ ጥናት አሰባሰብኩ።

ከUNDP እና ከአለም ባንክ በወጣው የማገዶ ፍጆታ ጥናት መሠረት 93.4% የሚሆነው ፍጆታ ከማገዶ እንጨት፣ ከከሰልና ከባዮ ጋዝ ሲሆን 6.6% ከሌላ ኃይል ነው። የአለም ባንክ ባለሙያዎች ጥናት ደግሞ 2 ኪሎ ግራም ደረቅ እንጨት አንድ ሰው በአንድ ቀን እንደሚጠቀም ጠቁሟል። የዓመት የማገዶ እንጨት ፍጆታችንም 23.83 ሚሊዮን ሜትር ኩብ እንደሚሆን ተገምቶ ነበር።

የማገዶ ወጭን በተመለከተ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ያለውን ማገዶ መግዛት የማይችለውን ግለሰብ ሳንጨምር መካከለኛው ቤተሰብ ከሚአገኘው ገቢ ከ20-25% የሚሆነውን ለማገዶ ያወጣል የሚል ግምት አለ።

ይኸውም መንግሥት ከህዝብ ከወረሳቸው ደኖች ላይ የባሕር ዛፍ ማገዶ ለአንድ ሜትር ኩብ ከ20 እስከ 58 ብር ድረስ ይሸጥ በነበረው ዋጋ ታስቦ ነው። በሕገ ወጥ የሚመረቱ ከሰሎች ደግሞ አንዱ ጆንያ (በግምት 60 ኪሎ ግራም የሆነውን) እስከ 70 ብር ይሸጥ ነበር። ነገር ግን በጋምቤላና በተመሳሳይ ቦታዎች ከሚገኘው የሱዳን ሣር የሚመረተው ማገዶ (FUEL BRIQUETTE) 100 ኪሎ ግራሙ ግን ከ20 እስከ 25 ብር እማምረቻው አካባቢ መሸጥ ይቻል ነበር። ምክንያቱም ሣሩን በነፃ ወይም በርካሽ ማግኘት ይቻላል። ወይም ይህንኑ ፊዩል ብርኬት ከተለያዩ ገለባዎችና ሣሮችም ማምረት ይቻላል። ሆኖም በመሐል አገር ግባቶችን እንደልብ ማግኘት ስለማይቻል የተፈለገውን ያህል ማገዶ በመጠነኛ ዋጋ ማግኘት አዳጋች በመሆኑ የማምረቻ ዋጋውም ሆነ መሸጫ ዋጋው ከፍተኛ እንደሚሆን አያጠያይቅም። ማገዶውን እስከ አዲስ አበባ ድረስ አምጥቶ በከሰል ዋጋ ቢሸጥ ትርፋማ መሆኑ ተረጋግጧል።

የማምረቻው መሣሪያዎች በተለያዩ አገሮች ይገኛሉ። እኔ ለጥናቴ የወሰድኩት ከሕንድና ከዴንማርክ ማኑፋክቸሪንግ ኩባንያ ሲሆን፣ ከአቅማችን ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ነው ያገኘሁት። በሕንድ The National Small industries Corporation Limited የሚያመርተውን ነበር እንደ ሞዴል የወሰድኩት።

ለምሳሌ ፋብሪካውን ለመትከል፦

1) ጠቅላላ የሚፈለግ ቦታ 1000 ሜትር ካሬ
2) በሕንፃ የሚሸፈነው መገልገያ ቤት 200 ሜ/ካሬ
3) የኤሌክትሪክ ኃይል 24 ኪሎዋት
4) ማንኛውም የጠራ ውሃ
5) ተፈላጊ መገልገያዎች፣ ቢሮ፣ ከሰል ማስቀመጫ መጋዘን፣ የጥገና ክፍል፣ የሚመረቱ ሣሮች ጥሬ እቃ መጋዘን ነው።

6) ፋብሪካው የሚኖረው ዋናው ቴክኖሎጂ ሣሩን የሚፈጭ፣ ወንፊት፣ ማድረቂያ፣ ፊዩል ሪኬቱን የሚአመርተው መሣሪያ ነው።
7) የሰው ኃይል፣ ልምድ ያለው 3 ሰው እና 3 ረዳቶች ብቻ ሲሆን ባጠቃላይ ስድስት ሰው ያስፈልጋል።
8) ፋብሪካውን ለመግዣና ለሥራ ማስኬጃ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር ያስፈልግ ነበር።
9) የምርት መጠኑ ደግሞ - በሰዓት ከ350 ኪሎ ግራም በላይ በአንድ ፈረቃ በ8 ሰዓት ወስጥ ከ2900 ኪሎ ግራም በላይ ያመርታል።

ማገዶው ከፍተኛ የማሞቅ ኃይል ያለው ሆኖ አመድና ጭሱ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ በማንኛውም ቤትና ቦታ መጠቀም የሚቻል ነው።

### የሱዳን ሣር ለቺፕውድ (Chipwood) መሥሪያ ማዋል፣

የሱዳን ሣር ጥራትና ጥንካሬ ያለው ቺፕውድ ለመሥሪያ ከሌሎች የግብርና ተረፈ ምርቶች በብዙ መልኩ የተሻለ ሁኖ አግኝቼዋለሁ።

ይኸውም:-

1ኛ/ ሣሩን በጋምቤላ፣ በኢሎባቦርና በከፋ ክፍለ ሐገር ውስጥ የተፈለገውን ያህል ማግኘት መቻሉ፣

2ኛ/ የተለያየ ዓይነት ቺፕውድ ለመሥራት ሣሩን በሚፈለገው ደረጃ ለመከርተፍ ቀላል በመሆኑ፣

3ኛ/ ሣሩን በተፈለገው ብዛት በጣም ርካሽ በሆነ ዋጋ ለመግዛት በመቻሉ፣

4ኛ/ የቺፕውድ ተፈላጊነት ከቀን ወደ ቀን እያደገ በመሄዱ በጣም አትራፊ ንግድ ከሚባሉት አንዱ ሊሆን በመቻሉ፣


5ኛ/ የአገሬውም ሕዝብ ሣሩን አጭዶ ቢያቀርብ ሰፊ የሥራ እድል ከማግኘቱም በላይ ስለማገዶ በጠቀስኩት ላይ በደን ምንጣሮ ምክንያት በከንቱ የሚቃጠለውን ሣር ለአገር ኤኮኖሚ በተለይም ለክፍለ ሐገሮቹ የማይነጥፍ የገቢ ምንጭ የሚያገኝበትን በር የሚከፍትለት በመሆኑ ኢንቨስተሮች በፊትም ሆነ አሁን ጥሬ እቃው በሚገኝበት ቦታ በርካታ ፋብሪካዎችን ማቋቋም ያስችላቸዋል።

እኔ ይህችን ማሳሰቢያ በዚህ ጽሁፌ ውስጥ ልጠቅሰው የፈለግኩት ፋብሪካዎቹን ወደ አገራችን አምጥቶ ቺፕውድ ለማምረት የሚያስፈልገው ካፒታልና ድካም ከውጭ አገር በየጊዜው የተዘጋጀውን ቺፕውድ ለማምጣት ከሚአስፈልገው ገንዘብና ውጣ ውረድ ይቀላል ብዬ ስለማምን እነዚህን ለአገር ጠቃሚ የሆኑትን ፕሮጀክቶች አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ኢንቬስተር በማቋቋም ሥራ ላይ እንዲረባረቡበት በአንክሮ ለመጠየቅ ነው።

## 5. መደምደሚያ

የ1966 ዓ.ም ለውጥ ብዙ ያስተማረን ስለሆነ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በጥቂት ሰዎች ስህተት ምክንያት የደረሰበትንና የሚደርስበትን በደልና ግፍ እያስታወሰ ለመበቀል ቢፈልግ ውጤቱ በበለጠ የሚጎዳው ንፁሁን ኢትዮጵያዊ ወገኑንና አገሩን መሆኑን ተገንዝቦ ደግ ነገርን ከመሥራትና ከማሰብ እንዳይቆጠብ በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይጠብቅ፣ ፈሪሐ እግዚአብሔርንም ያሳድርብን።


የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡
የ ር ሻ ፡ ሚ ኒ ስ ቴ ር ።

ቁጥር ፡
አዲስ ፡ አበባ
ቀን ፡ ፲፱፻፷ ዓ ፡ ም ፡